ለወጠባት ። አስናቀች ልታስቀይመው ስላልፈለገች በዘዴ ያዘችው ። ሙዚቃ ከፍቶ እንደንስ ሲላትም እሽ አለችው ። ቀስ በቀስ ጡቷን ፣ ጉንጯን እየዳበሰ ሊስማት ሲል ፊቷን ዞር አደረገችበት ። ስልት ቀይሮ ስሜቷን ለመቀስቀስ በተለያየ መንገድ ሞከረ ። ሁኔታው ቅር ቢያሰኛትም ስሜቱን ላለመጉዳት ስለፈለገች አላ ማው እንዳልገባት መስላ ታየች ። በግልፅ ሲቀርባት ግን በትዝብት አየችውና ፣ "ታዲ ፣ እኔ እኮ የማይህ እንደ ወንድሜ ነውና በሚያልፍ ከንቱ ነገር ስንገነባ የኖርን ውን ዝምድና አናፍርስ" አለችው ። እሱ ግን ቅን አነጋገሯ አጉል መግደርደር ስለ መሰለው ፍላጎቱን መግታት አቃተው ። አዝማሚያው ስላላማራት ክፉም ሳትናገረው ቀስ ብላ ከክፍሉ ወጣች ።

ታደሰ በእኔነቴ ብትንቀኝ ነው ብሎ ተበሳጨ ። የለም ሊሆን አይችልም ፤ ወንድምነቴን ስለ ፈለገች ነው አለ ። ያም ሆነ ይህ በፈፀመው ስህተት ሲፀፀት አደረ ። በሷ ላይ በነበረው የተሳሳተ ግምት ራሱን በራሱ አወገዘ ። በደረሰበት ውርደት በጣም አዘነ ። የሃፍረት ማቅ ለብሶ አይኗን ላለማየት ሲሸማቀቅ ውሎ አደረ ። አስናቀች ግን የነበረ ግንኙነታቸው በዚህ ምክንያት እንዳይሻክር ስለ ፈለገች ሆነኝ ብላ ጠበቀችው ። ተደብቆ ሊገባ ሲል አገኘችውና ፣ "ከልብህ አስበህበት ሳይሆን በመጥዎ ግፊት ያደረከው ነውና እርሳው" አለችው ። ታደሰ ቀስ በቀስ የሃፍረት ስሜት እየለቀቀው ሲሄድ ወዳጅ ነታቸውን በሞቀ መንፈስ አድሰው እስከ እለተ ሞቷ ድረስ ኖረዋል ።

ታደሰ ከመቃብር በታች የዋለ ውበቷን በአይነ ህሊናው ቃኘው ። የታፈነ ፍትወታዊ ስሜት በሷ ላይ ነበረውና ለዘላለም መታጣቷ አስቆጨው ። የተደበቀ

ፍላጎቱ ግቡን ሳይመታ በሞት መቀደሙ እንደ እሳት አቃጠለው ። ምናልባትም ይህ ስሜቱ ሊሆን ይችላል ሳያውቀው ራሷን በራሷ መግደሏን እንዳይቀበል ያደረገው ፤ ከጥርጣሬ ውስጥ ከቶ ያስጨነቀው ። ግን ከዚህ ውጭ ሌላ ምክንያት ከኖረው ከሱ በስተቀር ማንም አያውቀው ...

ስ ም ን ት

ማርታ ጠዋት ተነስታ ወደ ፍርድ ቤቱ የሄደችው በግርማ መፈታት እርግጠኛ ሆና ነው ። የቀጠሮውንም ቀን በናፍቆት የጠበቀችው በዚህ ምክንያት ነው ። የአስናቀች ራሷን በራሷ መግደል ጉዳዩን ግልፅ ስላደረገው ግርማ በነፃ ለመለቀቁ ቅንጣት ያህል አልተጠራጠረችም ። ይህ የሷ ብቻ እምነት ሳይሆን የብዙዎቹ ግምት ነው ። ስለሆነም ማርታ የዛሬዋን ቀን ከግርማ ጋር በደስታ አብረው ለማክበር የሚያስችል እቅድ አውጥታለች ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያወጣት የተጋበዘችበትን ሆቴል ምን ጊዜም ታስታውሰዋለች ። በምግቡ ጣእም ብቻ ሳይሆን በመስተንግዶውም በጣም ወዳዋለች ። ለእንዲህ አይነቱ ቀን ተስማሚ ቦታ ከዚያ የተሻለ የለም ብላ መርጣዋለች ። ለእስፈላጊው ወጭ የሚሆን ገንዘብም ከአባቷ ተቀብላለች ። በሰዎች ሴራ የተቋረጠ ፍቅራቸውን ለማደስና ለሱ ያላትን ስሜት ለመግለፅ ስለ ቸኮለች ሰአቱ አልንቀሳቀስ አላት ። ትእግስት አስጨራሽ ሆኖ መንፈሷን ረበሸው ።

ቀስ በቀስ ሰዎች ወደ አዳራሹ ገቡ ። የግርማ እናትም መጡ ። የለበሱት ቀሚስና ኩታ በአይነቱ ምርጥ

ስለሆነ የብዙዎቹን አይን ማረከ ። ደስታቸው ከገፃቸው ላይ ይነበባል ። የአስናቀችን ሞት የሰሙ እለት በቅርብ ባያውቋትም አዝነውላታል ። በሌላ በኩል ግን የልጃቸውን ስላግቢነት የሚያረጋግጥ ስልሆነ ደስ ብሏቸዋል ። ፍርድ ቤት ከመቅረቡ ፀሬት ልጃቸው እንደማይፈታ የሚመለከተውን ከፍል ጠይቀው በቅድሚያ ተረድተዋል ። ያም ፪ሆን ወዳጅ ዘመዶቻቸው ከቤታቸው ድረስ እየመጡ እንኳን ደስ አለዎት ብለዋቸዋል ። በበኩላቸው ለዛሬው የምስራች ቀን የሚሆን አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገዋል ። በጣም የሚቀርቧቸውን እንዳትቀሩብኝ ብለው መልእክት አስተላልፈዋል ። ልጇ ዳግመኛ ተመልሶ አደፍርስ ቤት አይገባም ብለው ወስነዋል ። ቤቱ ራሱ ገፌ ነው ብለው አምነውበታል ። ለዚህም ምክንያት ነበራቸው ። ለቤቱ መሰረት ሲቆፈር ጥቂት ማሪያ ቴሬዛ ብርና የኢጣሊያን ሊሬ ፀእንስራ ተቀብሮ ከቀን ሰራተኞች ውስጥ አንዱ ያገኛል ። ሌሎቹ እንዳያውቁበት ወዲያው አፈር ያለብስና ስራውን ይቀጥላል ። እስኪመሽ ይጠብቅና አውጥቶ ሊወስድ ሲል ቀን መደበቁን ያየው ባልደረባው ከቦታው ይደርሳል ። እንዴት እንደሆነ አሁን ትዝ አይሳቸውም እንጂ በሁለቱ ሰዎች መሃል አለመግባባት ተፈጥሮ ስለ ተደባደቡ እንደኛው ፀዚህ ጠንቅ መሞቱን ያስታውሳሉ ። የሳቸውም ወላጅ እናት ከትውልድ ሀገራቸው ለህክምና መጥተው ፀይወታቸው ያለፈው ከዚሁ ቤቅ ውስጥ ነው ። ስለዚህ ለጤንነቱም ሆነ ለህይወቱ ፈፅሞ እንደማይበጀው ሊያስረዱት አስበዋል ። ምክራቸውን እንደሚቀበል በማመን ቦታ መርጠው ከፊት ለፊት ከሚገኙት መንበሮች ከአንዱ ላይ ተዝናንተው ቁጭ አሉ ። የዳኛውንም መምጣት በናፍቆት ጠብቁ ።

ጠበቃው ማንደፍሮና አቃቤ ህግ በታቸውን ያዙ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ዳኛው ሲገቡ ሁሉም ብድግ ብሎ በአክብሮት ተቀበላቸው ። ተመቻችተው ተቀመጡና ተከሳሹ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጡ ። ግርማ ከእጃቢው ፖሊስ ጋር ወደ ውስጥ ሲዘልቅ ብዙዎቹ በፈገግታ ተመለከቱት ። ጠልተውት የነበሩትም በልባቸው ይቅርታ ጠየቁት ። ሳያውቁ በስሜታቸው ተገፋፍተው ፀፈፀሙት ስህተት የህሊና ወቀሳ የደረሰባቸው ጥቂት አይደሉም ። በተለይም የሞት ቅጣት ሲወሰንበት ለመስማት ጓጉተው የነበሩ ሁለት ጡረታ የወጡ አዛውንቶች በጣም ተፀፀቱ ። ግርማ ወደዚህ ለመምጣት ሲነሳ የእስር ጓደኞቹ በመፈታቱ እርግጠኞች ሆነው ያሳዩት ፍቅርና ያደረጉለት አሸኛኘት ልቡን ነክቶታል ። ዳግመኛ ወደ እኛ አትመለስምና ሲያመችህ ጠይቀን ስላሉት ታል ነብቶላቸዋል ። አጥር ግቢውን ወጥቶ እስኪሄድ ድረስ በአይናቸው ሸኝተው በመንፈስ ተከትለውታል ። ግርማ እውነቱ የሚገለፅበት ሰአት መድረሱ እየተሰማው ቁጭ አለ ። ዙሪያውን ሲቃኝ ከወትሮው የተለየ ገፅታዎች ማየቱ የሞራል ብርታት ስለ ሰጠው በውስጡ ያቆጠቆጠውን ተስፋ አለመለመው ። ከአሁን አሁን ጥሩተኛ አይደለሀም ብለው ሊያሰናብቱኝ ነው ብሎ ዳኛው ላይ አተኮረ ። ግርታም የሰዎች ስሜት ተለውጠ በርህራሄ አይን ስላዩት በጣም ደስ አላት ። የብሩህ ተስፋ ምልክት መሆኑ ተሰማት ። ስለዚህ ትክክለኛ ፍትህ ሲበየን ለመስማት ተቁነጠነጠች ።

ዳኛው በፍርድ ተግባር ላይ ከተሰማሩ ጀምሮ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥማቸው የመጀመሪያ በመሆኑ ግር ብሏቸዋል ። ሆኖም ከአንድ ውሳኔ ላይ ከመድረሳቸው በፊት ግራ ቀኙን ማከራከር አስፈላጊነቱ

ግልፅ ሆናላቸዋል ። በዚህ መሰረት ስለ አስናቀች ድን
ገተኛ ሞት በማንሳት አንዳንድ አስተያየቶች ሰነዘሩና
በቅድሚያ የአቃቤ ህግን ሀሳብ ጠየቁ ።

አቃቤ ህግ ተነሳና ፥ "ወይዘሮ አስናቀች ራሷን በራሷ
ለማጥፋት የተገደደችበት ምክንያት ገና በውል ባይታ
ወቅም ፥ በተከሳሹ ጠበቃ ተሰንዝሮባት በነበረው ውን
ጀላ ሳይሆን አይቀርም ብለን እንገምታለን ። ሆኖም
ግን የወይዘሮ አስናቀች ራሷን በራሷ መግደል በሞራል
ረገድ በደረሰባት የመንፈስ ጭንቀት እንጂ ከባለቤቷ
ከአቶ አደፍርስ ሞት ጋር ፈፅሞ አይዛመድም ። ስለዚህ
ፍርድ ቤቱ ይህን ተገንዝቦልኝ አስፈላጊውን ውሳኔ
እንዲሰጥ እጠይቃለሁ" ብሎ ተቀመጠ ።

ግርታ በከባድ ነገር ጭንቅላቷን የተመታች ያህል
ተሰማት ። ሰውም ወንበሩም ሲሽከረከር ታያት ። ሁሉም
ነገር የሚገላበጥ መሰላት ። የአቃቤ ህግ አነጋገር ክፉኛ
አበሳጫት ። ተነስተሽ ጉሮሮውን እነቂው አላት ። እልህ
እንደ እንጨት አደረቃት ። ለመሳደብም ቃጣት ። በግ
ርማ ህልውና የሚቀልድ መሰላት ። ወንጀለኛ መሆኗ ሲደ
ረስባት ከህግ ለመሸሽ ስትል ራሷን መግደሏ የአደባባይ
ምስጢር መሆኑ እየታወቀ እንዴት ግንኙነት የለውም
ይላል ብላ አርር ድብን አለች ። ይህ ሌላ ተልእኮ ቢኖ
ረው ነው በማለት ተቆጨች ። ሆን ተብሎ ግርማን ለመጉ
ዳት የተደረገ ተንኮል ነው ብላ አመነች ። በልቧ እየ
ተራገመችና እያወገዘች ቁና ቁና ተነፈሰች ። ምንም ለማ
ድረግ እንደማትችል አወቀችና ሳትወድ በግድ አርፋ

ተቀመጠች ። የሷን ያህል ስሜታቸውን ባይጎዳውም ሌሎ
ቹም ያልጠበቁት ሆነና ግር አላቸው ። ነገሩ ሁሉ እንቆ
ቅልሽ ሆነባቸው ። የተከሳሹ ጠበቃ በዚህ ነጥብ ላይ
አስተያየት እንዳለው ዳኛው ጠየቁት ።

ግንደፍሮ ከተቀመጠበት ተነስቶ ካባውን እያስተ
ካከለ እጅ ነሳና ፥ "በመሰረቱ የአቶ አደፍርስ መገደ
ልም ሆነ የወይዘሮ አስናቀች ድንገተኛ ሞት ሊነጣጠል
የማይችል የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ስለሆነ አስና
ቀች ራሷን በራሷ ለመግደሏ የተጨበጠ ማስረጃ አስካል
ቀረበ ድረስ በደንበኛዬ ላይ የሚሰጠውን ማንኛውንም
የፍርድ ውሳኔ እቃወማለሁ" በማለት ተናግሮ ቁጭ አለ ።

በአቃቤ ህግ አስተያየት የተገረሙት ታዛቢዎች
በግንደፍሮ አቀራረብ ይበልጥ ግራ ተጋቡ ። ራሷን ለመ
ግደሏ ማስረጃ ያስፈልጋል እንዴት ይላል አሉ ። የእን
ቅልፍ መድሃኒት በብዛት ቅማ ነው ተብሎ ተወርቷል ።
የሰማው ሁሉ አምኖበት ጉድ ሲል ከርሟል ። የሰሞኑ
የውይይት አርእስት ሆኖ ሰንብቷል ። አሟሟቷ የማያ
ከራከር ስለሆነ ብዙዎቹ ትክክል ነው ብለው ተቀብለ
ውታል ። እሱ ግን ማስረጃ ይቅረብ ማለቱ ላለመሸነፍ
የፈጠረው ዘዴ ነው ተባለ ። ጥያቄው አግባብ የለውም
የሚል ነቀፋ ተሰነዘረ ። ምናልባት የራሱ የሆነ ምክን
ያት ይኖረው ይሆናል ያሉት ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው ።
በቅጥ አዳምጠነዋል የሚሉ አንዳንድ ሰዎች ራሷን በራሷ
አልገደለችም ለማለት ፈልጎ ይሆናል ብለው ተጠራጠሩ ።
ሌሎች ግን ማስረጃው ቀረበም አልቀረበም የሚሰጠው
ጥቅም የለም ሲሉ አቋም ወሰዱ ። ከእንግዲህ ወዲያ

ህጋዊ ክርክሩ ወዘ አይኖረውም በማለት የተቹም ነበሩ ። በዚህ ምክንያት ኤዳራሹን ጥለው ልመውጣት የቃጣችው አልታጡም ።

የግርማ እናት ሁለቱን የህግ ሰዎች ታዘቧቸው ። ቋንቋቸው ራሱ ልዩ ሆነባቸው ። የማያስፈልግ አጉል ፀጉር ስንጠታ መልላቸው ። ባሏን በጽብቅ ገደለች ፤ ሲኦ ቃባት ደግሞ ፈራችና ራሷን ገደለች ፤ እንዲህ ቁልጭ ያለውን ነገር ለማጣመም መሞከር ለምን አስፈለገ ብለው ተቆጡ ። ሲያደንቁት የከረሙትን ጠበቃ በአይናቸው ገርፈው ገላመጡ ። ምንም ላይፈይድ ገንዘቤን ሲበዘብዝ ከረመ ብለው ተቆጩ ። ማርታም ብትሆን ክሳቸው የተለየ ስሜት አልነበራትም ። ሁለቱም የሚሰሩትን የሚያውቁ አልመሰላትም ። ለነገር የተፈጠሩ ነገረኞች በመሆናቸው ነው እንጂ በሰው ህይወት አያፈዙም ነበር በሚል ግምት ናቀቻቸው ። እንደ እንስሳት በስሜታቸው የሚመሩ ደካሞች አድርጋ ቆጠረቻቸው ። በተለይም ጠበቃውን አንቅራ ተፋችው ።

ዳኛው የደረረሰውን ፀጥታ አረጋግተና ፣ "ከወንጀል ምርመራ ክፍልና ከሠኪም የተገኘ መረጃ ካለ አቃቤ ህግ ለፍርድ ቤቱ ያቅርብ" ሲሉ ትእዛዝ ሰጡ ።

"ሀኪሞች የመርዝነት ባህሪይ ያለው መድሀኒት መሰዳ ነው ቢሉም ለህይወቷ መጥፋት ምክንያት የሆነውን ለማወቅ የሚያደርጉትን ምርመራ ገና አላጠናቀቁም ። ፖሊሶች ግን አንድ ብልቃጥ ከወይዘሮ አስናቀች መኝታ ቤት ኮሞዲኖ ላይ አግኝተዋል ። በብልቃጡም ውስጥ ያሉት እንክብሎች የእንቅልፍ መድሀኒት መሆናቸውን ልረጋገጠዋል ። ይህ መድሀኒት ደግሞ ከመጠን በላይ ከተወሰደ በህይወት ላይ አደጋ እንደሚያደርስ

ግንም ያውቃል ። ስለዚህ ህይወቷን ፀራሷ እጅ ለግጥ ፋቷ ከዚህ የተሻለ ማስረጃ ያስፈልግ አይመስለኝም ። ሆኖም ጠቃሚነቱ ይኖረዋል ከተባለ ግን ውጤቱ እንደ ተላከልኝ ለፍርድ ቤቱ አቀርባለሁ" በማለት አቃቤ ህግ አስረዳ ።

ጠበቃው ግንደፍሮ በዚህ እንደግጅስግግ ተቃውሞውን አሰምቶ የዳኛውን ፈቃድ በመጠየቅ ተነሳና ፣ "የመርዝነት ጠባይ ያለው ጎጂ ነገር መስዳ ይሆናል ማለትና የእንቅልፍ መድሀኒት ካላግባብ ከተጠቀሙበት በህይወት ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል መባሉ ፤ አስናቀች በመርዝ ወይም ከመኝታ ክፍሏ በተገኘው መድሀኒት ህይወቷ ጠፍቷል ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ይመስለኛል ። ስለዚህ ራሱን የቻለ መርዝ ወይም የእንቅልፍ መድሀኒት ህይወቷን ለመቅሰፉ በንጥረ ነገር ደረጃ ተለይቶ በምርመራ መረጋገጥ እንደሚናርበት ፍርድ ቤቱም ያምንበታል ብዬ እገምታለሁ" ሲል ሀሳቡን ገለፀ ።

ዳኛው ገባኝ በሚል ሁኔታ ራሳቸውን ነቀነቁና ፣ "የተጠቀሰው መርዝም ሆነ የእንቅልፍ መድሀኒት የየራሳቸው የሆነ የህይወት ቀላፊነት ባህሪይ እንዳላቸው ግልፅ ነው ። ወይዘሮ አስናቀች ከሁለቱ በአንደኛው መሞታ በጥናት የተረጋገጠ ማስረጃ ማስፈለጉን ፍርድ ቤቱም ያምንበታል ። ስልዚህ በአቃቤ ህግ በኩል ጉዳዩ ተጣርቶ በአስቸኳይ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ አዞአል አሉ ።

"ፀትእዛዙ መሰረት ይፈፀማል ። ሆኖም ግን አስናቀች በመረጠችው ተጠቅማ ህይወቷን ካጠፋች የመድሀኒቱ (ራሱን የቻለ መርዝ ከክፍሏ አልተገኘም) በጉጥ ነገር ደረጃ ተለይቶ መታወቁ ራሷን ፀራሷ አለመሞደ

ኗን ሊያመለክተን አይችልም ። ይህ ግልፅ እስከሆነ ድረስ የተከሳሹ ጠበቃ ከዚህ ውጭ የመከራከሪያ ነጥብ አለኝ ካሉ ያስረዱ ። እንዲሁም ራሷን አልገደለችም የሚሉም ከሆነ አቋማቸውን ግልፅ እንዲያደርጉ እጠይቃለሁ'' በማለት አቃቤ ህግ ለፍርድ ቤቱ አመለከተ ።

ዳኛው ክርክሩ ከጭብጡ ውጭ አፈንግጦ የማይ ፈለግ ውዝግብ እንዳያስከትል የተከሳሹ ጠበቃ በዚህ በኩል ያለውን አቋም ለፍርድ ቤቱ እንዲያስረዳ አዘዙት።

ጠበቃው ከወንበሩ ተነስቶ በዝግታ እርምጃ ወደ መሃል ገባና ዙሪያውን በአይኑ ቃኘ ። ከማርታ ጋር አይን ለአይን ግጥም ሲሉ ፈገግ አለ ። እሷ ግን በፈጠረው ውዥንብር ቅር ብሏት ነበርና ኮስተር ብላ ፊት ነሳችው። ከሁኔታዋ ስሜትዋ ስለ ገባው ጣራ ጣራውን እያየ ሀሳቡን በአንድነት ሰበሰበና ፣ ''አቶ አደፍርስ በልጃቸው ተገደሉ ፤ አስናቀችም ራሷን በራሷ ገደለች የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ያልተቀበልኩት በተለያዩ ምክንያቶች ነው ። በመሆኑም ነጥቦቼን ለፍርድ ቤቱ ግልፅ ለማድረግ ወደ ኋላ መመለስ ግድ ሊሆንብኝ ነው ። ስለዚህ ፍሬ ነገሩን ለመዳሰስ እንዲያመቸን ከመነሻው እንጀምራለን ። በተ ከሳሹና በወላጅ አባቱ መሀል የሀሳብ ልዩነት እንደ ነበረ ተረድተናል ። ይህ ቅራኔ ያስከተለው ፀብ ደግሞ አጥፊና ጠፊ አደረጋቸው ተብለናል ። በዚህ ከተማመን ወንጀሉ በተፈፀመበት አለት በነገር አለመግባባት እንደ ነበረ ከክፍላቸው ሲወጣ በሩን ካለአግባብ መዝጋቱ በምስክር ተረጋግጧልና አያከራክረንም ። ሀቁ ይህ ከሆነ ወንጀሉ የተፈፀመው በደም ፍላት እንጂ ቅድመ ዝግ ጅት ያልተደረገበት ለመሆኑ ከሁኔታው ለመረዳት አያ ዳግትም ። ግን ከተጨፈፈ የቃላት ጦርነት በኋላ ከሚች ክፍል የሚገኙት ቁሳቁሶች በሙሉ ቦታቸውን ሳይለቁ ፣

አቶ አደፍርስም ራሳቸውን ለመከላከል ምንም አይነት ሙከራ ሳያደርጉ ፣ ለመስዋእትነት እንደሚቀርብ እንስሳ አጎንብሰው አንገታቸውን ለካራ ሰጡ ማለት አንችልም ። ምክንያቱም የወንጀሉ ትክክለኛ ገፅታ ይህ አይደለምና !

''በመሰረቱ የወንጀሉም መንስኤ ነው የተባለው ምክንያት በቂ ካለመሆኑም በላይ ተከሳሹ ከአባቱ ጋር በፈጠረው አለመግባባት ህይወታቸውን ሊያጠፋ አስቦ ይሆናል ብንልም እንኳ በር በርግዶ ፣ ካራ መዞ የጥፋት እጁን በወላጅ አባቱ ላይ እንዴት ሊያነሳ ይችላል? ይህ ከሆነ በአቃቤ ህግ ከቀረበው የክስ ማመልከቻ ጋር ይቃረናል ። ለማንኛውም ወደፊት ስለምመለስበት ይህ በእንዲህ እንዳለ ሊቆይ ይችላልና በሌላ በኩል ያለውን እንመልከት ። አስናቀች ለፍርድ ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል ውስጥ እጠቅሳለሁ ፣ '....በሩ በሀይል ሲዘጋ ሰማሁ ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባለቤቴ ወደነበሩበት ክፍል ብሄድ ቁጭ ካሉበት ተገድለው በማየቴ ሀሊናዬን ሳትኩ ...' ነው ያለችው ። ግን ካለአግባብ የዘጋውን በር በመጀመሪያ ሳትከፍት የተፈፀመውን ድርጊት እን ዴት ለማየት ቻለች? ነጥቤን ግልፅ ለማድረግ ተከሳሹ በሩን ወርውሮ የዘጋው ስለሆነ ሳትከፍተው ከእርቀት የባሏን መሞት ልታይ አትችልም ። ስለዚህ ...'' ብሎ ሊቀጥል ሲል ፣—

ዳኛው ጣልቃ ገቡና ፣ ''እዚህ ላይ በሩ በሌላ ሰው ካልተከፈተ ያየችውን ማየት አትችልም ነበር ለማለት ነው የፈለከው?'' ሲሉ በመገረም ጠየቁት ።

ማንደፍሮ ቅንጣት ያህል ሳያቅማማ ፣ ''አዎ ፣ ማሳ የትም የፈለኩት ይህንኑ ነው ። አቶ አደፍርስንም ሆነ አስናቀችን የገደላቸው በሩን የከፈተው ሶስተኛው ሰው ነው'' በማለት መለሰላቸው ።

"ምን?" አሉ ዳኛው የሰሙትን በመጠራጠር ።

"ወንጀለኛው ሶስተኛው ሰው ነው" አለ ፈገግታ እያሳያቸው ።

"ዘዚህ አባባል ወይዘሮ አስናቀች ወንጀለኛውን ታውቀው ነበር ማለትህ ነው?" አሉ ፥ አሁንም በመ ገረም አይን አይኑን እየተመለከቱ ።

"አዎ ፥ ታውቀዋለች ፤ ወንጀሉንም ሲፈፅም አይታ ለች" ሲል በእርግጠኝነት መለሰላቸው ።

አቃቤ ህግ ተቃውሞ በማሰማቱ ዳኛው ምክንያቱን እንዲያስረዳ ስለ ፈቀዱለት ተነሳና ፥ "የተከሳሹ ጠበቃ ያልሆነውን የሆነ በማስመሰል ነገርን በነገር ሸርበው የከርክሩን ጭብጥ ለማጥፋት ካልሆነ በስተቀር ወይ ዘሮ አስናቀች የባለቤታን ገዳይ ካወቀች በምን ምክን ያት ሳትናገር ቀረች? ይህ እስካልተብራራ ድረስ ሶስተኛ ሰው የሚለውን መላምት ፍርድ ቤቱ ሊቀበለው አይገ ባም" ሲል ከሀይለ ቃል ጋር ተናግሮ ተቀመጠ ።

ዳኛው በአቃቤ ህግ አነጋገር ደስ አላላቸውም ነበ ርና ፥ "መቀበልም ሆነ ያለመቀበል የፍርድ ቤቱ መብት መሆኑ መታወቅ አለበት ። ለማንኛውም የተከሳሹ ጠበቃ በዚህ ነጥብ ላይ አስተያየት ካለው ለፍርድ ቤቱ ያሰማ" በማለት አዘዙ ።

"እስኝ ፤ ሆኖም ግን ማብራሪያም ሆነ ማስረጃዬን ላቀርብ የምችለው የአስናቀች ትክክለኛ እሚጃች ሲረጋገጥ ብቻ ነው ። ምክንያቱም ተቀባይነት የሚኖ ረው በዚያ ጊዜ ስለሆነ በዚህ በኩል የፍርድ ቤቱን ትዕ ብር በትህትና እጠይቃለሁ" አለ ጠበቃው ፥ ከተቀመጠ በት ተነስቶ እጅ በመንሳት ።

አቃቤ ህግ በድንገት ብድግ አለና ፥ "ወይዘሮ አስ ናቀች በሌላ ሰው ለመገደሏ በአካባቢ ማስረጃም ሆነ በምስክር አልተደገፈም ። ስለዚህ ትክክለኛ አሟሟቷ የተባለው ነጥብ ከጉዳያችን ጋር ስለማይገናኝ ጥያቄው እንዲሰረዝ እጠይቃለሁ" ብሎ አመለከተ ።

ዳኛው ስነስርአት ባለማክበሩ አቃቤ ህግን ገሰፁ ትና ፥ "ፍርድ ቤቱ የአቃቤ ህግን ተቃውሞ አልተቀበ ልውም ። ምክንያቱም የተከሳሹ ጠበቃ ክርክር የተመ ሰረተው ደንበኛዬ ለተከሰሰበት ወንጀል ተጠያቂው ወይዘሮ አስናቀችን የገደለው ሰው ስለሆነ ይህ ግልፅ ሳይሆን ማስረጃ ማቅረቡ ፍሬ የለውም ባይ ነው ። ነውን አይደልም?" ሲሉ ጠበቃውን እየተመለከቱ ጠየቁት ።

ግንደፍሮ እጅ ነሳና ፥ "ትክክል ነው" አለ በት ህትና ።

ዳኛው ሁለቱን የህግ ሰዎች በየተራ እየተመለ ከቱ ፥ "የማስረጃው መቅረብ ለመከላከያ ወሳኝነት ይኖ ረዋል ከተባለ የምርመራው ውጤት በሚመጡት አስር ቀኖች ውስጥ ሊደርስ ይችላል የሚል ግምት አለን ። ሰፋ ያለ ጊዜ የሰጠነውም ከአስከሬኑ የተወሰደውን ናሙና መርምሮ ለመጥቷ ምክንያት የሆነውን በንጥረ— ነገር ደረጃ ልይቶ ይህ ነው ለማለት ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን በመገንዘብ ነው ። ስለዚህ የሚቀጥለው ቀጠ ሮአችን የካቲት ሁለት ቀን እንዲሆን ተወስኗል ። ስለ ሆነም አቃቤ ህግ ጉዳዩን ተከታትሎ በተባለው ቀን ለፍርድ ቤቱ እንዲያቀርብ ታዞአል ። በቀኑ ቀጠሮው ችሎቱ ግራ ቀኙን ሰምቶ ማስረጃዎችን መርምሮ አስፈላጊ ውን ውሳኔ ይሰጣል" ብለው ተነሱ ።

በአዳራሹ የነበረው ህዝብ የሰማውን ማመን አት ቶት ረዘዘ ። ዳኛው ወጥተው ሲጄዱለት እንጂት ሊሆን

ይችላል ብሎ እርስ በርሱ ተንሾካሾከ ። በዛሬው ቀን ፍፃሜ ያገኛል ተብሎ የተገመተው ጉዳይ እንደገና ጥሬ ሆነ። ነገሩ በሰዎች መሀል የሀሳብ ልዩነት ፈጠረ ። ብዙዎች በግልፅ ተጨቃጨቁ ። ስለ ህግ እናውቃለን የሚሉትም በቡድን ተከፍለው አተካራ ያዙ ። አንዱ ሌላውን ለማ ዳመጥ ስላልቻለ ከፍርድ ቤቱ እየተጨቃጨሁ ወጡ ። ቅጥር ግቢውን ለቀው እስኪወጡ ድረስ አንዱ ሌላውን ለማሳመን የጦፈ ክርክር ገጠሙ ። የአቃቤ ህግ ደጋፊ የሆነው ወገን የአስናቀች ሀይወት ያለፈው በመርዝ ቢሆ ንም እንኳን በፈቃዷ የጠጣችው ወይም የዋጠችው ስለ ሆነ ሌላ ወንጀለኛ ሊኖር አይችልም ብሎ ተሟገተ ። ተከራካሪው ክፍል መልስ አጣና ዝም አለ ። ሽንፈትን በፀጋ ከማይቀበሉት አንዱ ጣልቃ ገባና እስገድደዋት ይሆናል የሚል አስተያየት ሰነዘረ ። ከሞት የከፋ ምን ሊመጣባት ተገዳ መርዝ ትጠጣለች ተብሎ ስል ተፈዘ በት አፈረ ። በዚህም ክርክሩ በአቃቤ ህግ ደጋፊዎች አሸናፊነት ተደመደመ ።

ግርታ ስታልመው የከረመችው ሁሉ ከመነሻው ቶርሽ ስለሆነባት በሽቃ ህጋዊ ክርክሩን በቅጥ አላዳ መጠችም ። አልፎ አልፎ የሰማችውም ፍሬ ያለው አል መሰላትም ። ከፍርድ ቤቱ ውጭ በጉዳዩ ላይ ሰዎች ሲጨ ቃጨቁ ብታይም ተጠግታ ልታዳምጣቸው አልፈ ለገችም ። ማንደፍሮን በርቀት ብታየውም ልታነጋግረው ስላልፈለገች ፊቷን አዙራ አቅጣጫዋን ቀየረች ። ሶስ ተኛው ሰው ከሚለው ጋር ገደል ይግባ ብላ በልቧ እየተ ራገመች ወደ ቤቷ ሄደች ።

የግርማ እናት ግን ጠበቃው ከፍርድ ቤት እስኪ ወጣ ድረስ ጠብቀው አነጋገሩት ። ምነው እንዲህ አደ

ረከኝ ብለው ወቀሱት ። ቅሬታ እንዳደረባቸው ቀደም ሲል የገባው ቢሆንም ምን አጠፋሁ አላቸው ።

"አስናቀች ራሷን በራሷ የገደለችው በባለቤቷ ላይ በፈፀመችው ወንጀል ተፀፅታ ነው ብለህ ብትከራከር ኖሮ ልጄ በነፃ ይለቀቅ ነበር ። ጥሩ መጥተህ እንዲያው ከዚህ ላይ ስትደርስ ምን ነካህ!" አሉ ፥ መከፋታቸውን በገፃቸው ላይ እያስነበቡት ።

ማንደፍሮ ተሳስተዋል ሊላቸው አልደፈረም ። እን ኳን እሳቸው ብዙ ያውቃሉ የተባሉትም አስናቀች ህይ ወቷን አላጠፋችም ብሎ መከራከሩን እንዳልወደዱለት ያውቃል ። የሱን ሀሳብ ያልደረሱበት ስለሆነ ሲልፈረደ ባቸውም ። የመረጠው መንገድ ትክክለኛ መሆኑን ሊያ ስረዳቸውም አልሞከረም ። አቅጣጫውን የለወጠበትን ምክንያት ቢገልፅላቸውም ነገሩ አሁን ተንጠልጥሎ ያለ በት ሁኔታ ስለማያመች አምነው አይቀበሉትም ። ስለ ዚህ ከህሊናው ጋር መከረና ፥ "በእናትነትዎ ለልጅዎ ደህንነት ቅድሚያ እንደሚሰጡ ይገባኛል ። ይህም መሆን ያለበት ነው ። እኔም ለቆምኩለት ሰው ያለብኝ ግዴታ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ደግሞ ይበልጥ የማስ በው ለሙያዬ ክብርና ለእውነት ልእልና ነው" አላቸው ፈገግ ብሎ ።

"እውነቱማ አደባባይ ወጣ ፤ ከዚህ ወዲያ እውነት ከወዴት ሊመጣ !" አሉ በመገረም አይን አይኑን እየ ተመለከቱ ።

"ሊመስልዎ ይችላል ፤ ብቻ እውነቱ ግና ከተቀበ ረበት አልወጣም "ሲል መለሰላቸው ።

"ወንጀለኛው ሌላ ሰው ነው ማለትህ ነው እውነቱን!" አሉ በማሽሟጠጥ መልክ ።

"አልተሳሳቱም ፤ ደርሰውብታል" አለ ፥ እሱም እንደ ቀልድ አድርጎ ።

"እውነት ሌላ ሰው ነው ወንጀለኛው ብለህ ክልብህ ታምናለህ ?" ሲሉ ፀመጠራጠር ጠየቁት ።

"አዎ!" አላቸው ።

"ጸኛው ፥ ለመሆኑ ሌላ ነቃሽ ቁጠር ቢሉህ ከየት ታመጣለህ?" አሉት ።

ግንደፍሮ በሴትየዋ የዋህነት ፈገግ አለና ፥ "ክቤ ታቸው" ሲል መልሰላቸው ።

የግርማ እናት አላመኑትም ነበርና ፥ "ግን እንዳሰብ ከው ያልሆነ እንደሆነ ምን ታደርጋለህ?" በማለት ጠየቁት።

"ያን ጊዜ ለልጅዎ ሌላ ጠበቃ ይፈልጉ እልዎታ ለሁ" አለ ፥ ኮስተር ብሎ ።

"ይህማ ትክክል አይደለም !" አሉ ፥ በአንጋፃሩ ተደ ናግጠው ።

"በእኔ ላይ እምነት ካጡ ሌላ ምርጫ የለኝም ።"

"እንደሱ እኮ ማለቴ አልነበረም ልጅ ግንደፍሮ ፤ ብቻ የሴትየዋ ወንጀለኛነት ከታወቀ ሌላ ጣጣ ውስጥ ገብተህ ለምን ትደክማለህ ነው አባባሌ" አሉ ፥ በመለ ማመጥ መልክ ።

"ወንጀለኛ አይደለችም" አለ ፥ ፈርጠም ብሎ ።

"ካልክ ይሁና! እንዲያው ብቻ ድካምህ አላዘንኩ" አሉ ነገሩ ካንጀታቸው ጠብ ስላላለ ።

"ክእንግዲህ ወዲያ ምንም ድካም አይኖርብኝም ፤ ስላሰቡልኝ አመሰግናለሁ ። ልጅዎም ቢሆን በቅርብ ቀን ውስጥ ይፈታል የሚል እምነት ስላለኝ እስከዚያው ድረስ ፀትእግስት ይጠብቁ ፤ ለማንኛውም በቸር ይግጠ ጠመን" አልና ተሰናብቷቸው ወደ መኪናው አመራ ።

የግርማ እናት ሌላ ወንጀለኛ አለ ብለው ስላላመኑ በሰጣቸው ተስፋ ብዙም አልረኩ ። የማያስፈልግ የሚቅ ጭቅ ምእራፍ ከፍቶ ልጇን ባያጉላላው ደግ ነበር አሉ። ደህና ሄዶ ሄዶ መጨረሻው ላይ ስላበላሸ አዘኑ ። አንዳ ንድ ጠበቆች ጥቅማቸው እንዳይቋረጥ ሆን ብለው ነገር ያጣምማሉ የሚለውን ሀሜታ አስታወሱ ። ማንደፍሮም ጉዳዩን የጎተተው ይህን አስቦ ይሆናል ብለው ተጠራጠሩ። በፀሳባቸው አውጥተው አውርደው እንዲህ አይነት ልክ ስክስ ሰው እንኳን አይመስለኝም ብለው ራሳቸውን ወቀሱ ። በባህሪውና በችሎታው የተመሰገነ ሰው በሀይ ወት እንደማይነግድ ተስፋ አደረጉ ። ይህም ባይሆን ግን ያለቀለት ጉዳይ እንደገና ወደ ኋላ ሊመለስ ነው ብለው ሰጉ ። በወንጀለኛውም መገኘት እርግጠኛ ሳይሆኑ ቀሩ ። ያልታሰበ ነገር በመፈጠሩ እየተቆጩ ወደ ቤታቸው ሄዱ።

ግርማ የሁለቱን የህግ ሰዎች ክርክር ሲሰማ ነው ተስፋው የጠወለገው ፤ ሞራሉ ደቆ ስሜቱ የላሸቀው ። የጠበቀው ቀርቶ ያልጠበቀው በመሆኑ አዘነ ። እየተ በሳጨ ከወህኒ ቤቱ መኪና ውስጥ ገብቶ ተቀመጠ ። ፀኔታውን ከተመለከቱት የህግ አስረኞች አንዱ ምን ተመሰንብዘ ሲል ጠየቀው ። መልስ ሳይሰጠው እንዳቀረ ቀረ ዝም አለ ። እየንተንተ ሰላም ስለነሳው የሆነውን ነገረው ። ታዲያ ይህ ምን ያስከፋል ያስደስታል እንጂ አለው ። ግሮግ በሰውየው በሽቆ ባልሰራውት ወንጀል

ከዚህ ወዲያ ምን እደረጋለሁ ብሎ ተናገረው ። ሰውየው ፈገግ አለና አንድ ተረት እንዳጫውትህ ፍቀድልኝ ብሎ ጠየቀው ። ግርማ ቀጥል በሚል ሁኔታ ቀና ብሎ አየው።

"ሁለት ወንበዴዎች በጥፋታቸው ከፍርድ ቤት ቀርበው እድሜ ልክ እስራት ተፈረደባቸው ። አንዱ ይግባኝ ሲል ባልደረባው የባሰ አታምጣ በማለት ፀለየ ። ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በስቅላት እንዲቀጡ ወሰነ ባቸው ። እንደኛው እንደ ልማዱ ይግባኝ ሲጠይቅ ጓዳኛው ግን የባሰ አታምጣ አለ ። ባልደረባው ተበሳጭቶ ከሞት የባሰ ሌላ ምን ሊፈርዱብን ይችላሉና ነው የባሰ አታምጣ የምትለው ብሎ ተቆጣው ። 'ተው እንጂ! ቁልቁል ተሰቅለው በርበሬ እየታጠኑ ይሙቱ ቢሉንስ?' አለው ይባላልና በዚህ በቀላሉ ነገር ልታዝን አይገባም በማለት ሰውየው ግርማን መከረው ። ተረቱ ለግርማ ስሜትም አልሰጠው ። እንዲያውም ከሱ ችግር ጋር የሚገናዘብ ስላልመሰለው እንዳልሰማ ሆኖ ችላ አለው ።

"ይህ ተረት ሳይሆን ያንተ ቅዠት ነው" አለ ፣ በለ ካፊነቱ የታወቀው እስረኛ ።

"እንዴት?" ሲል ሰውየው ጠየቀ ።

"ለእውነት አትከራከር የሚል ተረት የለማ!" አለ።

"ቀጣፊ ደግሞ ስለ እውነት ምን ያውቃል!"

"ቀጣፊ ማነው?"

"አንተው ፤ ንገሩኝ ባይ ፤ የታሰርከውም በማጭበርበር ነው ። "

"ልብ አድርጉልኝ ከርከሮ ሲሰድበኝ!" አለ ዙሪ ያውን በፈዝ መልክ እየተመለከተ ።

የሰውየው ግራና ቀኝ ያሉት ሁለቱ የውሻ ክራንቻ በመባል የሚታወቁት ጥርሶች ከከንፈሩ ወጣ ወጣ ያሉ በመሆናቸው እስር ቤቱ ውስጥ የተሰጠው የቅፅል ስሙ ነው ። ከርከሮ ብሎ የሚጠራው ሰው ጠላቱ ነው ። በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ ተደባድቧል ።

ወዲያው ደሙ ፈላ ። ሰውነቱ ተለዋወጠና ተቆጣ። ብድግ ብሎ ለካፊውን ሊያንቀው ሲል ግርማ ከጎኑ ስለነበረ እጁን ቅፍድድ አድርጎ ያዘው ። አራስ ነብር ሆኖ ለገላጋይ አስቸገረ ። ካልገደልኩት ብሎ ተጋበዘ ። ከመኪናው ውስጥ ሰላም ደፈረሰ ። ደግነቱ ፖሊሶቹ ነገሩን ወዲያው አበረዱት ። ይጠበቁ የነበሩት እስረኞች ስለ መጡ ጉዞ ወደ ወህኒ ቤት ሆነ ።

ዘ ጠ ኛ

ግንደፍሮ ጠዋት በአስራ ሁለት ሰአት እየተነጫነጨ ከመኝታው ላይ የግዱን ተነሳ ። የቀሰቀሰችው ባለ ቤቱ አልማዝ ነች ። ለምን እንደ ቀሰቀሰችው ምክንያቱን ያወቀው በኋላ ነው ። ከአራት ቀኖች በፊት የሙታን ሀውልት መርቁልን የሚል የጥሪ ካርድ እንደ ደረሳቸው ትዝ አለው ። ግንኑታችንን እወቁልን ለማለት ሰውን እንቅልፍ መንሳት ምን ይባላል አለ አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ራሱን እያከከ ። ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ይህን የመሰለው ጥሪ ደርሶት አልተቀበለውም ። ግብዝነትና አጉል ጉራ ነው ብሎ ንቆ ትቶታል ። በዚህ ምክንያትም ብዙ ሰዎች ተቀይመውታል ። አንዳንዶቹ በግልፅ አኩርፈውታል ። እሱ ግን በሞኝነታቸው ሰቆባቸዋል ። ከአልልማዝ ጋር ከተጋቡም በኋላ በዚህ ጉዳይ ብዙ ተጨቃ

ጭቀዋል ። ሰው ሁሉ ባህላችን ነው ወጋችን ነው ብሎ ያመነበትን አንተ ብቻህን ትከከል አይደለም ልትል አይገባም ብላዋለች ። ለቋሚውም ሆነ ለሚቹ የሚሰጠው ጥቅም ስለሌለ ሊነቀፍና ሊወገዝ የሚገባው ልማድ ነው ብሎ ቢከራከርም አልተቀበለችውም ። ብለቅሶ ባህል የተኳሳ ትዳራቸውን ከሚፈታተን ቅራኔ ላይ ደርሰው እንደነበረ ያስታውሳል ። ለጠባቸው መንስኤ የሆነው የአክስቷ ባል ወንድማቸውን ተረድተው ሀዘን ይቀመጣሉ ። የሰሙ እለት ለቅሶ ይደርሳሉ ። የእዝንም ይወስዳሉ ። በሶስተኛው ቀን ሌሊት ተነስታ ሳልስት እንሂድ አለችው ። ብለን ብለን ደግሞ ለመርዶም ሳልስት ፈጠርንለት? አሁንስ ቅጥ አጣን ብሎ ተመልሶ ተኛ ። ባለቤቱ አልማዝ በዚህ ተቀይማ ጠዋት እንደ ወጣች ወደ ቤቷ ሳትመለስ ቀረች ። ግቷ ከቤተሰቦቿ ዘንድ ቢሄድ አራስ ነብር ሆነው ጠበቁት ። እንዴት እንዲህ ይደረጋል ብለው ተቆጡት ።

በመጨረሻም ከዘመድ ከወዳጅ የሚያቀያይም ወን ጀል በመፈፀሙ ተወቅሶ ፤ ወደፊት እንዲህ አይነት ህገ ወጥ ድርጊት ላይፈፅም ቃል ገብቶ ሚስቱን ይዞ ተመለሰ።

ሚቹ በዳኝነት ስራ ለረጅም ዘመን ስላገለገሉ ማን ደፍሮ ያውቃቸዋል ። ባሰፈራቸውም የተከበሩ አዛውንት ናቸው ። ከልጃቸውም ጋር የቅርብ ግንኙነት አለው። ሀውልታቸውን ለመመረቅ የተገደደው ግን ሚስቱን በመፍራት ነው ። ውስጥ ውስጡን እየበሸቀ ልብሱን ልበሰ ። ከሙታን አምባ ሲደርሱ ስፍር ቁጥር የሌለው ሰው መቃብሩን ከቦ ቆሟል ። ሀውልቱ በክሬል በጥቁር ጨርቅ ተሸፍኗል ። የሚቹ የህይወት ታሪክ የተፃፈበት መለስተኛ መፅሄት የሚያህል ጥራዝ ይታደላል ። ቀሳ

ውስቱ በዜማ ይፀልያሉ ። የሚቹ ቤተ ዘመዶች ሳይቀሩ እርስ በርሳቸው ይወያያሉ ፤ ቀልድ እየፈጠሩ የሚስቁም ነበሩ ። አልማዝ የምታውቃቸውን ሴቶች በሩቅ አይታ ኖሮ ሄዳ ከነሱ ጋር ተቀላቀለች ። ማንደፍሮ የተሰጠውን መፅሄት እያገላበጠ አንዱን የመቃብር ሀውልት ተደግፎ ቆመ ። ልባሱ ላይ ያለው ፎቶ ሚቹ በጎልማሳነታቸው ዘመን የተነሱት ነው ። በወዳጃቸው የተፃፈው መግቢያ የሚቹን ደግነት ፣ ሀገር ወዳድነት ፣ አዋቂነት ፣ ትሁትነት ፣ ወዘተ. አጋኖ አቅርቦታል ። የልጆቻቸው ፣ የሚስታቸው ፣ የወንድም ፣ የእህታቸው ፣ የሀዘን እንጉርጉሮ ሰፊ ቦታ ቢሰጠውም በአንድ ሰው የተገጠመ ለመሆኑ በግልፅ ይታወቃል ። ሰው ራሱን እንዴት ያታልላል አለ ማንደፍሮ ግጥሞቹን ተመልክቶ ። በመፅሄቱ ውስጥ ሚቹ በግላቸው ፣ ከቤተሰቦቻቸውና ከቅርብ ወዳጆቻቸው ጋር የተነሱት ፎቶግራፎች በብዛት ይገኙበታል ። ከመጨረሻው ገፅ ላይ ካለው ምስላቸው ግርጌ ፤ "ለተራቁ ያበላ ፣ ለተጠማ ያጠጣ ፣ ለታረዘ ያለበሰ ታላቅ ሰው ለዘለአለም አንቀላፋ" የሚለውን ውዳሴ ተመልክቶ ማንደፍሮ ፈገግ አለ ። መቹ ይሆን ከፋ ሰው የሚሞተው ብሎ ፉሱን ጠየቀ ። እስከ መቹ ነው ባራሳችን የምንቀልድ አለ ።

ሁለት ፎቶግራፍ አንሺዎች ከሚመረቀው ሀውልት ግራና ቀኝ ከሚገኙ መቃብሮች ላይ ወጥተው ካሜራቸውን ቁልቁል ደቅኑ ። አንደኛው ቁስ በትልቁ መልቀል ሀውልቱን እየዞሩ ባረኩና ተመልሰው ቦታቸውን ያዙ። የሚች ንስሀ አባት በጣታቸው ምልክት ሲሰጡ ፀጥ ቁር ጨርቅ የተሸፈነው ሀውልት ተገለጠ ። ሴቱ ወንዱ እሪ ብሎ ጮኸ ። መፊት ቁና ሆነች ። ድምፁ ፀአካባቢው አስተጋባ ። የካሜራው መብራት ብልጭ ድርግም

አለ ። ሲያለቅስ ለመነሳት የፈለገው ወገን ወደ ክሜራው አንጋጠጠ ። እኔንም አትርሳኝ ያለ ፊቱን አጨማደዶ ፣ ጥርሱን አግጥጦ ፣ አንገቱን አጣሞ እንዳንጋጠጠ ቀረ ። እንባ አውጥቶ ያለቀሰ ግን አንድም አልነበረ ። ወዳጅ ዘመድ ነኝ ያለ ሁሉ በደረቁ አላዘነ ። ማንደፍሮ ወዲያው ስቆ ወዲያው ማልቀስ የተዋንያኖች ልዩ ስጦታ ይመስለው ነበር ። ግን ይህን ቀልድ አየና አስመሳይ ሁሉ ብሎ እርር ድብን አለ ።

የጨኸቱ ስነስርአት እምስት ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ተፈፀመ ። ወዲያው ሀዘን መሆኑ ተረሳና ሁሉም እየተጨዋወተና እየተሳሳቀ ቁርስ ለማድረግ ወደ ስንበቴው ቤት ተጓዘ ። ለሀውልት ምረቃ ሲባል የተዘጋጀውን ምግብ መብላት ትክክል ናቸውና በርቱ በት ብሎ ድጋፍ እንደ መስጠት ስለ ቆጠረው ማንደፍሮ ወደ አዳራሹ መግባት አልፈለገም ። ወቀሳቸውን በመፍራት ብቻ መምጣቱን ለማሳወቅ ሲል ከሀዘንተኞቹ አንዱን ጠብቆ እጅ ነሳ ። ፊቴን ካስወጋሁ ይበቃል ብሎ ሊወጣ ሲል ከበሩ ላይ የቆመው አስተናጋጅ ሻይ እንኳን ሳይቀምሱ እንዴት ብለው ይሄዳሉ ብሎ አከላክለው ። ከሱ ጋር ሲጨቃጨቅ አንድ ሰው በስሙ ጠራው ። ዞር ሲል ታደሰ ብርሃኑን አየው ።

ታደሰ ወደ ዩኒቨርስቲ ሲገባ ማንደፍሮ የአራተኛ አመት የህግ ተማሪ ነበረ ። ለአጭር ጊዜ ቢሆንም በአንድ መኝታ ቤት ውስጥ አብረው ኖረዋል ። ግቢውን በማለማመድም ሆነ ቤትምህርቱ ስለ ረዳው ማንደፍሮን ይወደዋል ። በችሎታውም ያደንቀዋል ። በስራ አለም ከተሰማሩም በኋላ ታደሰ አንዳንድ ችግር ሲገጥመው ያማክረዋል ። የቀረበ ወዳጅነት ባይኖራቸውም በተመሳሳይ ሙያ የተሰማሩ ስለሆኑ ይገናኛሉ ። አልፎ አልፎም አብረው ይዝናናሉ ። ከሰላምታ በኋላ በታደሰ አግባቢነት ተያይዘው ወደ ስንበቴው አዳራሽ ገቡ ። ቁርስ ይሁን እንጂ ስሙ የተዘጋጀው ለምሳ የሚሆን ምግብ ነው ። ቦታ ለማብቃቃት ሲባል የሚበላው ቆሞ ነው ። ከጥቂት ጊዜ በፊት ሀዘነተኛ የነበሩት ብሉልኝ ጠጡልኝ እያሉ ሽር ጉድ ሲሉ ፣ በደማቅ ፈገግታ ሲጋ ብዙ ፣ ወጣት የሆኑት ሴቶች የሚያውቁትን ወንድ በአይን ጥቅሻ ሲያግባቡ የተመለከተ ለሰርግ በአል የተጠራ ቢመስለው አያስደንቅም ። ማንደፍሮ አንድ ስኒ ሻይ ይዞ ከዚያ ሁሉ የምግብ አይነት ምክንያት እየሰጠ ከአንዱም ሳይቀምስ ቀረ ። ጠላም ጠጅም ያመኛል አል ጠጣም አለ ። ዙሪያውን በትዝብት አይን ቃኘ ። ያሰቃቹ ሁኔታ በጣም አስገረመው ። ከዚያም አልፎ ስለ አበሳ ጨው ፣ "ጉድ ነው!" አለ ሳያስበው ።

"ምኑ?" ሲል ታደሰ ጠጋ ብሎ ጠየቀው ።

"የፈጠራ ችሎታችን ነዋ!" አለ ድምፁን ዝግ አድርጎ ።

"እንዴት?" አለው ።

"ስንኩል አላማ በሚያራምዱ የመንደር ሴቶች መረዳጃ በሚል ሽፋን በተቋቋመ ማህበር አማካኝነት ከቀብር መልስ ሶስት ቀን ከትሞ መብላት ። እንደምታየው ደግሞ የመቃብር ሀውልት አስመርቆ እየበሉ እየጠጡ መዝናናት ። እነዚህ በከፍተኛ ጥረት በቅርብ የተገኙ የፈጠራ ውጤቶች ናቸው" አለ እንደ ፌዝ አድርጎ ።

ታደሰ ይህን አጉል ግብዝነት ባይደግፍም እንደ ማንደፍሮ አያወግዘውም ። እንዲያውም ሀብታም ሰዎች ቢያደርጉት ገንዘባቸውን የሚጥሉበት ስላጡ ይሆናልና

ሊፈፈድቸው አይገባም የሚል ነጥብ አነሳ ። ማንደፍሮ ግን ይዚህ ሀሳብ ፈፅሞ አልተስማማም ። "ሰዎች ከንቃተ ህሊና ዝቅተኛነት የተነሳ ከሚጠቅማቸው ደግ ነገር ይልቅ የሚጎዳቸውን ሳያውቁ በቀላሉ ይከተላሉ ። ስለዚህ ማህበረሰቡ የጥቂቶችን መጥፎ አርአያ እየተከተለ ሲሄድ በኑሮው ላይ ቀውስ ያስከትልበታል ። ይህም በትልህ እየታየ መምጣቱን ለማረጋገጥ ህዝን ቤት መመላለስ አያስፈልግም" አለውና በቅርቡ የገጠመውን አጫወተው ።

"ሰውየውን ከልጂነቱ ጀምሮ አውቀዋለሁ ። በአንስተኛ ገቢ የሚተዳደር የአራት ልጆች አባቅ ነው ። ከጥቂት ወሮች በፊት ባለ ቤቱ እድር ልባ ነው ። ትል ዋለች ። ስንክፍልበት የኖርነው ምን ሆነና ነው ይላታል ። ይህኛው የሴቶች ብቻ ስለሆነ ከአለን እድር ይለያል በማለት ታግባባውና የሰፈሩ የሴቶች ማህበር አባል ትሆ ናለች ። ከገንዘቡ መዋጮ ሌላ የእገሊት ባል አጎቱን ተረዳ ሲባል አስር እንጀራ ፤ እገሌት አያቷን ተረዳች አስር እንጀራ ። አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከቀለባቸው ላይ ሃምሳ እንጀራ ይነሳለታል ። ሰውየው አዝማሚያው ስላላማረው ይዚህ ሁኔታ ከቀጠልን ልጆቻችን በችጋር ያልታሉና ከዚህ አቆርቋዥ ማህበር መውጣት አለብሽ ይላታል ። ሚስት ግን በአንገቱ ገመድ ! አላደር ገውም ብላ አሻፈረኝ ትለዋለች ። ሰውየው በዚህ ተበሳጭቶ እንግዲያው ልጆቼን እያስራብኩ ወረ ሰማይ የም ቀልብበት ምክንያት የለኝም ይልና ያባርራታል ። ከአላ ግባብ ከቤቱ ወጣሁ ብላ ስለ ከሰሰችው ጉዳያቸው በቤ ተዘመድ ጉባኤ እየታየ ነው አለና ፤ ታዲያ ይህ ክምን የመጣ ይመስልሃል ?" ሲል ታደሰን ጠየቀው ።

"ክሞኝነት!" በማለት መለሰለት ።

"በንጠላው ስታየው ሞኝነት ይመስላል ፤ ግን ስረ መሰረቱ የአካባቢ ተፅእኖ ነው" አለ ማንደፍሮ ።

ታደሰ ጉዳዩን ሳያውቀው ቀርቶ ሳይሆን ማንደፍሮን ላናግረው ብሎ ፤ "እንዴት ?" አለው ።

"እንዴት ብሎ ጥያቄ አይገባኝም ፤ ወዳጅ ዘመድ ላለ ማስቀየም ስትል የማታምንበትንና የምታውገዘውን ነገር ላትወድ በግድ ትፈፅማለህ" አለ ጥርሱን ነክሶ ።

ታደሰ መብሸቱን ተረዳና እውነትህን ነው በሚል ሁኔታ እንገቱን ነቀነቀ ። ወንዱም ሴቱም አፉን እየጠራረገ ከአዳራሹ መውጣት ጀመረ ። አልማዝ የጀመረች ውን ወሬ እስክትጨርስ ድረስ ክበሩ አጠገብ ቁመው ጠበቋት ። ፈገግታ እያሳየች ወደ ነሱ መጣችና ፤ "ግሩም ቁርስ ነበር ፤ ከሆነ አይቀር እንዲህ ነው !" አለች ።

ታደሰም ለድግሱ አድናቆቱን ገለፀ ። ማንደፍሮ ግን በልቡ ጅቦች ብሎ ተሳደበ ።

ታደሰ ባልና ሚስቱን ተሰናብቷቸው መንገድ ከጀመረ በኋላ አንድ ነገር ትዝ ስላለው ወደ እነሱ ተመለሰ ። ማንደፍሮ የመኪናውን በር ለመክፈት ቁልፍ ሲያወጣ ታደሰ ደረሰና ፤ "ሳልጠይቅህ እረስቼው ልሄድ ነበር፤ ለመሆኑ ሰምተሃል ?" አለው ።

"ምኑን?" ሲል እሱም ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ ።

"ስለ አስናቀች ሞት የሰማኸው ነገር የለም ?" አለ በመገረም ።

"የምርመራውን ውጤት እየጠበኩ ነው" አለ ለጉዳዩ ክብደት የሰጠው በማይመስል ሁኔታ ።

"በመርዝ መሞቷን አልሰማህም ?" አለ በመደነቅ ።

ማንደፍሮ ያሰበው ትክክል በመሆኑ ውስጥ ውስ ጡን ደስ እያለው ፥ "እርግጠኛ ነህ?" ሲል በፈገግታ ጠየቀው ።

"የእንቅልፍ መድሀኒት ሳይሆን የገደላት ራሱን የቻለ መርዝ መሆኑን ደርሼበታለሁ" አለ ተኩራርቶ ።

"ማን ነገረህ ?"

"ማን ቢሉህ ማን ታውቃለህ?" አለ በፌዝ መልክ።

"ቅልዱን ተወውና እንዴት ሰማህ ?" አለው እው ነት መሆኑን ለማወቅ ጓጉቶ ።

"በአንድ አጋጣሚ ምርመራውን ያከናወነውን ባለ ሙያ አግኝቼው ወዳጄ ስለሆነ ውጤቱን ነገረኝ ። ከተ ጠራጠርክ ሻምበል ታምሩን አነጋግረው ። ጉዳዩን ለማጣ ራት እየተሯሯጠ ነው" አለውና ደህና ዋል ብሎት ሄደ።

ማንደፍሮ በሰማው ዜና በጣም ተደሰተ ። በሀው ልቱ ምረቃ የሀዘን ጭጋግ ለብሶ የነበረው ገፁ ፈካ ። ከሙያ ጓደኞቹ አስናቀች ራሷን በራሷ አልገደለችም በማ ለት የመጀመሪያው ሰው ታደሰ ነው ። ከሚችታ ጋር ባለው ግንኙነት ጉዳዩን በቅርብ ከሚከታተሉት አንዱ እሱ ነው ። የማንደፍሮንም አቋም በመደገፍ ግንባር ቀደም ነው ። ስለዚህ የነገረውን አልተጠራጠረም ። መኪ ናው ውስጥ ገብቶ ሞተሩን አስነሳ ። አልማዝ የተነጋገ ሩትን የሰማች ቢሆንም ወሬውን ለማረጋገጥ ስለ ፈለገች ፥ "እውነት መርዝ ነው ተባለ?"ስትል አይን አይኑን እያ የች ጠየቀችው ።

በአምንታ መለሰላት ።

"እንዳሰብከው መሆኑ ድንቅ ነው ፤ ግን በህግ ፊት ጥቅሙ ምንድነው?" አለችው ።

በመርዝ መሞቷ በግልፅ መታወቁ የክርክሩን መልክ እንደሚለውጠውና በሰው መገደሏንም ፍርድ ቤቱ እንዲ ቀበለው አመች ሁኔታ እደሚፈጥርለት አስረዳት ።

አልማዝ ቀደም ሲል በዚህ ጉዳይ ላይ ከማንደፍሮ ጋር በሰፊው ተወያይታበታለች ። ሶስተኛ ሰው አለ የሚለውን የባሏን ፅንሰ ሀሳብ ሀሊናዋ ስላልተቀበለው ትክክል አይደለህም ብላ በድፍረት ተከራክራዋለች ። ራሷን በራሷ ለመግደሏ እርግጠኛ ስለሆንኩ እንወራረድ ብላዋለች ። የውርርዱ ገንዘብ ከግራ ወደ ቀኝ ኪስ መግ ባቱን አውቀሽ ነው ብሎ እንዳፈዘባት ታስታውሳለች ። በእንቅልፍ መድሀኒት ሳይሆን የሞተችው በመርዝ ነው ሲላት ስቃበታለች ። አሁን ግን እሷና ሌሎቹ እንዳ መኑበት ሳይሆን የአስናቀች ህይወት በመርዝ መጥፋቱ ሲረጋገጥ አፈረች ። ከሷ ችሎታ ውጭ የተወሳሰበ ነገር መኖሩን ለመቀበል ተገደደች ። በማላውቀውና ባልተ ረዳሁት ጉዳይ ሁለተኛ እልከራከርም ብላ ወሰነች ።

ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነገሩ ስለ ከነከናት ፥ "ወን ጀለኛው መርዙን አስገድዶ አጠጣት? ወይም ሳታውቅ ከምግቧ ላይ ነስንሶ ገደላት?" በማለት ጠየቀችው ።

"በሁለቱም መንገድ አይደለም" አላት ፈገግ ብሎ ።

"ይህ ካልሆነ እንዴት ሊገላት ቻለ?"

"በግምት እንደዚህ ነው የተገደለችው ልልሽ አል ፈልግም ። እንደ ሰማሽው ደግሞ ጉዳዩ ቀላል ስላልሆነ እውነቱ ላይ ለመድረስ የባለሙያዎችን እውቀትና ጥረት

ይጠይቃል ። ብቻ በሻምበል ታምሩ ችሎታ ቅለምተማ መን ወንጀለኛውን በቅርቡ እንደሚያጋልጠው እርግ ጠኛ ነኝና ያን ጊዜ ጥያቄሽ ትክክለኛውን መልስ ያገ ኛል" አላት ።

ከአልማዝ መስሪያ ቤት ክመድረሳቸው በፊት ፍንጭ ልመስጠት ያህል አንዳንድ ነጥቦች አስያዛትና ወንጀለኛውን ለማወቅ ደህና ሙከራ ካደረግሽ የወርቅ አንባር እገዛልሻለሁ በማለት ቃል የባላት ። አልማዝ በምንም ተአምር እንደማትደርስበት ስላወቀች ለአንድ አንባር ብዬ እንኳሌን አልበጠብጥም አለችው ። ማንደ ፍር የሚስቱ ብልጠት ስለገባው እየቀለደ ከቢሮዋ አድ ርሷት ሄደ ።

አ ስ ር

አስናቀች በመርዝ መሞቷን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ሻምበል ታምሩ በሀሳብ ሲባዝን ከረመ ። የወንጀሉን አመጣጥ እንደገና ከስር መሰረቱ ለማጥናት ሁኔታዎችን ክተለያየ አቅጣጫ ለመመርመር ሙከራ አደረገ ። የመ ጀመሪያው ከሁለተኛው ምንም ልዩነት እንደሌለው ተገነ ዘበ ። በተጨማሪም ማንደፍር ከቢሮው ድረስ መጥቶ ለወንጀሉ መፈፀም መሰረታዊ መንስኤ ነው ብሎ ያመ ነበትን ምክንያት በመግለፅ የሚይናቅ ፍንጭ ሰጠው ። ስለ መርዙም ባህሪ ከባለሙያዎቹ ሰፊ ማብራሪያ አገኘ ። መርዙ እንዴት ከወንጀለኛው እጅ ሊገባ እንደ ቻለ ለማወቅ የተደረገው ክትትል ግን አድካሚና ትእግስት አስጨራሽ ሆነ ። ያም ቢሆን ከወንጀለኛው ላይ ለመድ ረስ ከባድ መሰናክል እንደማይሆንበት አመነ ። ተጨባጭ

ሁኔታው ወደ አንድ አቅጣጫ የሚያመለክት ስለሆነ ወሳኝ ነጥብ ላይ ደረሰ ። ዝግጅቱን ካሟላ በኋላ ወደ አቶ አደፍርስ ቤት ሄደ ።

መላኩ የመኪና ድምፅ ሰምቶ ከሳሎኑ መስኮቶች የአንደኛውን መጋረጃ ሲገልጥ ሻምበል ታምሩን አየው። ሰውነቱ ሽምቅቅ አለና ብርክ ያዘው ። ለምን እንደ ደነ ገጠ ግን እሱም ራሱ አያውቀው ። ምን ሊያደርግ መጣ የሚለው ጥያቄ አእምሮውን በጠበጠው ። አቶ አደፍ ርስ የሞቱ ጊዜ እየተመላለሰ በጥያቄ እንዳስጨነቀው አስታወሰ ። ጥቃቅን ነገሮችን እንኳን በቸልታ የማያልፍ ጥብቅ መርማሪ መሆኑን ተገንዝቧል ። የፈለገው ነጥብ ላይ ለመድረስ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች አስደንቀው ታል ። ለአንድ ጥያቄ የተለያየ መልክ በመስጠት ለማ ሳመን የሚያደርገው ሙከራ አስገርሞታል ። መላኩ አውጥቶ አውርዶ የሻምበሉ አመጣጥ እንቆቅልሽ ሆነበት። በደህና እንዳልሆነ ቢሰማውም ምክንያቱ ግን አልገ ባውም ። ሰውነቱን ቢቀፈውም ምንም እንዳልተሰማው ሆኖ በሩን ከፈተና ተቀበለው ።

ሻምበል ታምሩ የወዳጅነት ጉብኝት ለማድረግ የመጣ በሚመስል ሁኔታ መላኩን በፈገግታ ጨብጦ ጤንነቱን ጠየቀው ። ብዙ ጊዜ እንደሚያውቃቸው የበቀ ለችንም ደህንነት ጠየቀና ተዝናንቶ ተቀመጠ ። ሲጃራ ውን ሲያቀጣጥል በቀለች መጥታ ሰላምታ ሰጠችውና ምን እግር ጣለህ ብላ እንደ ቀልድ ጠየቀችው ። ሻም በል ታምሩም ለቀላል ጉዳይ ሊያነጋግራቸው መፈለጉን ገለፀላቸው ። ወደ ፈለገው ነጥብ ክመግባቱ በፊት ስለ ሌላ ጉዳይ አንስቶ እነጋገራቸውና መላኩን እየተመለ ከተ ፥ "ዐእንተና በወይዘሮ አስናቀች መሀል ነበር የተፃ ለው ግንኙነት ፀእደባባይ ከተገለፀ በኋላ የመንፈስ ጭን

ቀት እንቅልፍ ስለነሳት መድሀኒት መውሰድ ጀምራ ነበር ተብሏል ። ግን ወይዘሮ አስናቀች ማህበረሰቡን የሚያስቆጣ ድርጊት ፈፅመሻል ተብላ መወንጀሏ ራሷን በራሷ እንድትገል የሚገፋፋ በቂ ምክንያት ነው ብለህ ታምናለህ?" ሲል ጠየቀው ።

"ባልተጨበጠ መነሻ ይሉኝታን ገፍትራ ፣ ትዳርን አደፍርሳ ፣ በባሏ ላይ ሸፍታ ይቅርታ የሌለው በደል ፈፅማለች ብሎ ክብረ—ህሊናዋን በፍርድ አደባባይ አር ክሶ በመወንጀል የገደላትን ያን አደናጋሪ ጠበቃ ለምን አትጠይቀውም ነበር!" አለ መላኩ በቁጣና በብስጭት ከመቀመጫው ዘሎ በመነሳት ።

በመላኩ አነጋገርና ሁኔታ ሻምበል ታምሩ ቅር ስላለው ፣ "አትሳሳት እንጂ አቶ መላኩ ! ወንጀሉ ሊፈፀም የቢቃው የሞራል ግዴታ በመጣሱ ነው አለ እንጂ ወይዘሮ አስናቀች የወንጀሉ ፈፃሚና ገዳይ ነች አላለም ። ስለዚህ በዚህ መንስኤ ብቻ ራሷን ገደለች ብለህ ታምና ለህ ወይ? ነው የኔ ጥያቄ " አለ ጥርሱን ነክሶ ።

መላኩ ሳያስበው በስሜቱ ተገፋፍቶ በፈፀመው ስህተት ወዲያው ስለተፀፀተ ይቅርታ ጠየቀውና ፣ "ሌላ ምክንያት የላትም" አለ እንደበቱን አለስልሶ ሲቀመጥ።

"እንቺስ?"አለ በቀለችን እየተመለከተ ።

በቀለች ጣቷ ላይ ያለውን የወርቅ ቀለበት እየደባ በሰች ፣ "እውነት ለመናገር ፣ የጠበቃው ዘለፋ ቅስሟን ነው የሰበረው ። አእምሮዋንም አናግቶት ነበር ለማለት ይቻላል ። እንዲህ አይነቱን ከባድ ርምጃ ለመውሰድም የተገደደችው ከምርጫ ማጣት ይመስለኛል" አለች በእ ርግጠኛነት ።

"አዎ ፣ ምርጫ አልነበራትም ፤ የሰው ህይወት የጠ ፋው በኔ ስህተት ነው ብላ አመነች ፤ የጥፋት ምንጭ ነኝ ብላ ራሷን አወገዘች ፤ ቅጣቱንም ራሷ ወሰነች ፤ የታሪ ኩም ምእራፍ ከዚህ ላይ እንዲዘጋ አደረገች" አለ መላኩ በከፍተኛ የሀዘን ስሜት ተውጦ ።

ሻምበል ታምሩ በድንገት ራሷን በራሷ አልገደለ ችም ሊላቸው ስላልፈለገ ፣ "አልመሰለኝም ፤ ታሪኩ መልክ ያዘ እንጂ አልተፈፀመም" አለ ፈገግ ብሎ ።

በቀለች ግራ በተጋባ ሁኔታ ሁለቱንም በየተራ ተመልከታ ፣ "ራሷን በራሷ መግደሏን ይጠራጠራሉ ማለት ነው ?" ስትል ጠየቀችው ።

"ፖሊስ ምንጊዜም ተጠራጣሪ ነው" አለ ፈገግ ብሎ ።

"የአስናቀች ሞት አጠራጣሪ ሊሆን!" አለ መላኩ በማፌዝ መልክ ።

ሻምበል ታምሩ ከተቀመጠበት በዝግታ ተነስቶ አንድ እጁን ከኪሱ ከተተና ጣራ ጣራውን እያየ ፣ "ከተ ጨባጭ ሁኔታ ብንነሳ ፣ ወይዘሮ አስናቀች አመንዝራለች ተብላ የተወቀሰችው ከአምስት ቀን በፊት ነው ። ስለዚህ ምስጢሩ በመገለፁ ተበሳጭታ ፣ በሀፍረት ተሰቃ ፣ በፍ ርሃት ተውጣ ፣ በበደሏ ተፀፅታ ከመኖር አለመኖርን ከመረጠች ፣ የዚያኑ እለት ማታ ህይወቷን ታጠፋለች እንጂ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንዴት ሳምንት ያህል ትቆያለች ? በሌላ በኩል ደግሞ ባለቤቷን ላለመግደ ሏና በሷ በኩል ተፈፀመ የተባለው ጥፋት ከሀግ አንፃር ምን መልክ እንደሚኖረው አስተያየት ለማግኘት የህግ ባለሙያ ባማከረች ማግስት ፣ ሀሳቧን ለውጣ ራሷን

በራሷ ገደለች ብንል የስነልቦና ተመራማሪዎች አይቀ በሉንም" አለ የሶፋውን ጠርዝ በሁለት እጆቹ ተደግፎ ።

"ምናልባት ያነጋገረችው የህግ ሰው አያዋጣሽም ብሏት ይሆናል !" የሚል አስተያየት በቀለች ሰነዘረች ።

ሻምበል ታምሩ እየተንጎራደደ ፥ "ደህና ገምተሻል ፤ ብቻ ሰውየውን ስላነጋገርኩት ተሳስተሻል "አላት ።

መላኩ ነገሩ ስላልገባው ፥ "ጠበቃ አነጋግራ ነበር ነው የምትለው?" ሲል በመገረም ፈዞ ጠየቀው ።

"አዎ ፥ ምናልባት ክስ ቢመሰረትብኝ ብላ የህግ ሰው አማክራ ነበር ። "

መላኩ ነፃሩ ስለከነከነው ፥ "ይገርማል!" አለ በረጅሙ ተንፍሶ ።

"ሁለታችሁም ይህን አታውቁም ነበር?" አለ ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ።

በቀለች ጭራሽ አልሰማሁም ስትል ፥ መላኩም ልነገሩ እንግዳ መሆኑን ገለፀለት ።

ሻምበል ታምሩ ወደ ሌላ ጥያቄ ከመሻገሩ በፊት እየተንጎራደደ ጥቂት አሰበ ። ሁለቱም አናውቅም ብለው መካዳቸው ተሰሩ አላስቆረጠውም ። እንዲያውም ከመነሻው ያደረበትን ጥርጣሬ አስወገደለት ። አለማወቃቸው አቀራረቡን እንዲያስተካክል ረዳው ። መላኩ አጠገብ ቆመና ፥ "በሁለታችሁ መሃል ምስጢራዊ ግንኙነት መኖሩን ጠበቃው ካጋለጠ በኋላ ወይዘሮ አስናቀች ያደረባትን የመንፈስ ጭንቀት ለማስወገድ በመድሀኒት መጠቀሟን ታውቅ ነበር?" አለ አይን አይኑን ትኩር ብሎ እየተመለከተ ።

"አዎ ፥ አውቃለሁ" በማለት መላኩ መልሰ ።

ሻምበሉ ፊቱን ወደ በቀለች መልሶ ፥ "አንቺስ?" አለ ።

"የእንቅልፍ መድሀኒት መውሰዷን አውቃለሁ" ስትል መለሰችለት ።

"በራሷ ውሳኔ ነው ወይንስ በናንተ በወዳጇ ምክር ?" አል በማሽሟጠጥ መልክ ።

ሁለቱም ተያይተው መልስ ሳይሰጡ ዝም አሉ ።

ሻምበል ታምሩ መልስ ስጡኝ ብሎ አሳስጨነቃቸውም ። ከኮት ኪሱ አንድ ትንሽ ብልቃጥ አወጣና ለሁለቱም በየተራ አሳያቸውና ፥ "ወይዘሮ አስናቀች ባደረባት የመንፈስ ጭንቀት የተነሳ እንቅልፍ በማጣቷ መሰቃየቷን በመገንዘብ ይህ መድሀኒት እንደሚረዳት በማወቅ ገዝታችሁ ሰጣችኋት" አለ በእርግጠኝነት ።

"በቀለች ይረዳታል ስላለችኝ መድሀኒቱን የገዛሁት እኔ ነኝ" አለ መላኩ ተቻኩሎ ።

"በብዙ ሀኪሞች የሚታዘዝ ፍቱን መድሀኒት መሆኑን ማንም ያውቃል!" አለች ተኩራርታ ።

"ጠቃሚነቱን እንጂ ጎጂነቱን ብዙዎቹ በውል አያውቁም"አለ ሻምበሉ ።

"ከመጠኑ እንዳያልፍ ከተጠነቀቁ ጉዳት አያመጣም" አልች ።

"ይህ ከሆነ አንድ ሰው በቀን ሊወስደው የሚገባውን ኪኒን ለወይዘሮ አስረድታችኋታል?" ሲል በቀለችን እየተመለከተ ጠየቃቸው ።

"እምነ" በማለት በቀለች መለሰችለት ።

"ስንት መውሰድ ነበረባት ?"

"ሁለት ብቻ " አለች ።

"ከመቸ አንስቶ ነው መድሀኒቱን መውሰድ የጀመረችው ?"

በቀለች ጥቂት አሰበችና ፥ "ከተወነጀለችበት ከጥር ሰባት ቀን ጀምሮ ይመስለኛል" አለች መላኩን እያየችው ።

"እቶ መላኩስ ?"

"በተባለው ቀን መጀመሯን አስታውሳለሁ" አለ ።

"ሁለታችሁም እርግጠኞች መሆናችሁ መልካም ነው ። ይኸኛውን ጥያቄ ልብ ብላችሁ እንድታዳምጡኝ እፈልጋለሁ ። ወይዘሮ አስናቀች ከጥር ሰባት ቀን ጀምሮ ህይወቷ እስካለፈበት ጥር አስራ አንድ ቀን ድረስ በየቀኑ ሁለት ሁለት ፍሬዎች ሳታቋርጥ ብትጠቀም በጠቅላላው የወሰደቻቸው ፍሬዎች ቁጥር ስንት ይሆናል ?" ሲል ጠየቃቸው ።

መላኩ እስቲ ላስበው አለና በጣቶቹ ለመቁጠር የግራ እጁን አውራጣት ለጥር ሰባት ቀን በማዋል አንድ ብሎ ጀመረ ። አመልካች ጣቱን ለጥር ስምንት ፣ መሃከ ለኛውን ለጥር ዘጠኝ ፣ የቀለበቱን ለጥር አስር ፣ ትንሿን ጣት ለጥር አስራ አንድ አድርጎ በመቁጠር በአምስት ቀኖች ውስጥ አስር ፍሬዎች መውሰዷን ገለፀ ።

"ልክ ነህ፣ ብልቃጧም የምትይዘው አስር ፍሬዎች ብቻ ነው ። ይህች ብልቃጥ ባዶ መሆን ሲገባት አሁ

ንም በውስጧ ሁለት ፍሬዎች አሉባት ። ጥያቄው እንዴት ሊሆን ቻለ ነው!" አለ ሻምበሉ ብልቃጧን እየተመለከተ ።

"ምናልባት አንድ ቀን ዘንግታው ሳትውጥ ቀርታ ይሆናል" አለች እጅዋን በእጅዋ እያሻሸች ።

"እውነትሽን ነው ፤ ዘንግታ ይሆናል ፤ ብቻ ግን በአራት ቀን ውስጥ ስምንት የእንቅልፍ መድሀኒት ፍሬ ዎች መውሰድ በሰው ህይወት ላይ አደጋ ሊያደርስ ይች ላል ?" ሲል በቀለችን ጠየቃት ።

"አይመስለኝም" አለችው ።

"በዚህ ከተማመን ወይዘሮ አስናቀችን ምን ገደላት እንላለን ?" አለ ሁለቱንም በትዝብት እየተመለከተ ።

"አንተ ንገረን እንጂ! እኛማ ምኑን እናውቃለን!" አለ መላኩ ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ።

"ሁለታችሁም አታውቁም ማለት ነው?" ሲል ፀመ ገረም ጠየቃቸው ።

"እንዴት ልናውቅ እንችላለን ?" አለች በብስ ጭት ።

ሻምበል ታምሩ ብልቃጧን መልሶ ከኪሱ ከተተና ፥ "ለቀባሪ ማርዳት ካልሆነብኝ ምን ከፍቶኝ !" አለና ሁለቱን በፈገግታ ተመለከታቸው ። ሲጃራ አወጣና አቀ ጣጠለ ። ጭሱን እያቦነነ ምንም ሳይተነፍስ ዝም አለ ። በቀለች ተቁነጠነጠች ። መላኩ ቀና ብሎ ተመለከተው ። ሻምበል ታምሩ ሲጃራውን ኮሰተረና ፥ "ወይዘሮ አስና ቀች ባለቤቷ ላይ የፈፀመችው በደል በይፋ ከታወቀ

በኋላ ጉዳዩ ከአቶ አደፍርስ ሞት ጋር የማይነጣጠል መሆኑን ስለተረዳች ፥ የሷ ተጠያቂነት እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ለማወቅ የህግ ችሎታ ያለውን ሰው ለማነጋገር መፈለጓን በጣም ለሚቀርባት ወዳጅዋ አማከረች እንበል!" አለና መላኩን አየው ።

"በፍፁም አላማከረችኝም" አለ ፀቁጣ ታል ።

ሻምበል ታምሩ ሳቅ ብሎ ፥ "እኔም አላልኩ አቶ መላኩ !ግን ይሀን ሀሳቧን በቅድሚያ የተረዳ ሰው የአቶ አደፍርስ አሟሟት ዝንተ አለም ተሰውሮ እንዲቀር ምኞቱ ነበርና ወይዘሮ አስናቀች የምታውቀውን ምስጢር ለህግ ጠበቃ ከመተንፈሷ በፊት አንደበቷን መዝጋት አስፈላጊ መሆኑን ስላመነበት ገደላት" አለ ጣራ ጣራውን አሻቅቦ እየተመለከተ ።

መላኩ በእልህ ይውን በፍርሃት ፥ እየተንቀጠቀጠ ፥ "እኔ እሷን ለመግደል ምክንያቅ የለኝም!" አለ ።

"ላይኖርህ ይችላል ብቻ ..." ብሎ የጀመረውን ሳይጨርስ ፥

በቀለች ጣልቃ ገባችና ፥ "እንቆ ነው የገደላት?" ስትል መላኩን በክፉ አይን እየተመለከተች ሻምበ ሉን ጠየቀችው ።

"አይደለም ወይዘሪት በቀለች! ጥር አስራ አንድ ቀን ወይዘሮ አስናቀች ከቤት ባልነበረችበት ወቅት ከቤ ልቃጢ ውስጥ የነበሩትን ሁለት የመጨረሻ ፍሬዎችን በማውጣት በምትኩ በአይነት ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት መርዘኛ ፍሬዎች ለውጦ ብልቃጢ ከነበረችበት አስቀ ምጦ ወጣ ። ወይዘሮ አስናቀች በመኝታ ሰአት እንደ

ተለመደው በሰላም ለመተኛት ፍሬዎቹን ውጣ ጋደም እንዳለች በዚያው ለዘላልም አንቀላፉች" በማለት አስ ረዳት ።

"በመርዝ!" አለች ግራ በገባ ሁኔታ እየተቅበጠበጠች።

"አዎ ፥ በመርዝ ተገደለች ! ሰውየው መሞቷን አረጋግጦ ሲነጋጋ ሲል የወሰደውን ሁለት ፍሬዎች ግንም ሳያየው መልሶ ክብልቃጢ ውስጥ አስቀመጠ ። ይህን ያደረገውም ተመርምሮ የአንቅልፍ መድሀኒትነቱ ሲረጋገጥ የሚያስተኛ መድሀኒት በብዛት ወስዳ ራሷን በራቂ ገደለች ተብሎ እንዲታመንለት ያደረገው ብልጠት ነበር ። ዳሩ ግን የህግ አይን ሲፈርጥ ፥ የእውነት ጆሮም ሊደነቁር የማይችል መሆኑን ባለመረዳቱ በድጋሚ ተሳ ቷተ" አለ በመስኮቱ ውጭ ውጭውን እየተመለከተ ።

መላኩ የሰማውን ማመን አቅቶት ፥ "በድጋሚ!" አለ ደንግጦ ።

"አዎ ፥ ለሁለተኛ ጊዜ ተሳሳተ" አለው ፊቱን ወደ እሱ መልሶ ።

"እንዴት? በድጋሚ ተሳሳተ ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው?" አለች ደከምከም ባለ ድምፅ ።

ሻምበል ታምሩ ወደ ቦታው ቀመልሶ ተቀመጠና ፥ "እንደገና ወደ ኋላ መመለስ ሊኖርብን ነው ። ሁኔታውን ስለምታስታውሱት ግር ይላችኋል አልልም ። ነገሩ እን ዲህ ነው ። ግርማ ያፀቱን ክፍል በር በቁጣ ዘግቶ ሲወጣ እቅ አደፍርስ በልጃቸው ክፉኛ ስለ ተበሳጩ የደም ግፊት ፀጋታቸው ይቀስቀሳል ። በዚህ ሳቢያም ስታይ ይደቸው ይጨነቃል ። ይህን እጋጣሚ ተዘጋጅቶ ሲጠ

ብቅ የቆየው ወንጀለኛ የእርዳታ እጁን የሚዘረጋ መስሎ ፍላጎቱን ለመፈፀም ወደ ክፍላቸው ይገባል ። አቶ አደ ፍርስ መድሀኒትና የሚውጡበት ውሀ እንዲሰጣቸው በምልክት ይጠይቁታል ። ሰውየውም የሚፈልጉትን መድ ሀኒት የሰጣቸው በማስመሰል ሌላ መርዛም ፍሬ በምትኩ ከውሀ ጋር ያቀርብላቸዋል ። በበሽታ ላይ መርዝ ሲታከ ልበት ውጤቱ ግልፅ ነውና ወዲያው ያዳክማቸዋል ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አቶ አደፍርስ በመርዙ እንደ ሚሞቱ ያውቃል ። ግን የሰውየው አላማ ግርማን በወ ንጀሉ ተጠያቂ ለማድረግ ስለነበር ጩቤውን ከማጅራ ታቸው ላይ ተክሎ ሲወጣ ከወይዘሮ አስናቀች ጋር ፊት ለፊት ይጋጠማሉ!" አለ በስሜት ተውጦ ሁለቱንም በየተራ እየተመለከተ ።

መላኩ ያ የሚዘገንን ሁኔታ እንደገና ከፊቱ ላይ ድቅን ሲልለበት ፊቱን በእጆቹ ሸፍኖ ፥ "በጭራሽ ሊሆን አይችልም! ፍፁም አላምንም!" በማለት ተወራጨ ።

"ምኑን ነው የማታምነው?" ሲል ሻምበሉ በመ ደነቅ ጠየቀው ።

"አስናቀች አይታው ዝም አትልም ፤ ውሸት ነው!" አለ እንባ እየተናነቀው ።

"የራሷ የሆነ በቂ ምክንያቱ ስለነበራት ዝም ማለት ነበረባት!" አለው ።

"የኔና የሷ ጥፋት ከሆነ ምክንያቱ ተሳስተሃል" አለ መላኩ አይኑን እያሻሸ ።

ሻምበል ታምሩ ተሳስተሃል የሚለው ቃል ከግናደድ ይልቅ አሳቀውና ፥ "ስህተት ከሆነ ትክክለኛ ምክንያቷን አንተ ንገረኛ!" አለ ከሳቁ ሳይገታ ።

መላኩ ከግንባሩ ላይ ያለው የደም ስር እንደ ቀንድ ቆመ ። ፊቱም ተለዋወጠ ። የሚናገረው ጠፍቶት ከን ፈሩ ተንቀጠቀጠ ። በቀለች አይናፋን ወደ ጣራው ላከች። ሻምበል ታምሩ ሁለቱንም በየተራ እየቃኘ ሁኔታቸ ውን ለማጥናት ሞከረ ። በመሃላቸው ሰፍኖ የነበረውን ፀጥታ የስልኩ የጥሪ ድምፅ አደፈረሰው ። ደግሞ ሲደ ወል በቀለች ሂዳ እነሳችው ። መለያ ቁጥሩን ተናገረች ። የአቶ አደፍርስ ቤት መሆኑን አረጋገጠች ። መነጋገራ ሪያውን በእጅዋ አፍና ጥሪው ለሻምበል ታምሩ መሆኑን ገለፀችለት ። ሻምበሉ ስልኩን ተቀብሎ ፊት ለፊቱ ባለው መስኮት ውጭ ውጭውን እየተመለከተ ንግግሩን ቀጠለ ። በጥሞና አዳምጦ አስፈላጊውን መመሪያ ሰጠና ስልኩን ዘጋው ። አስቸጋሪ ሆኖ የቆየ ጉዳይ ነበርና መፍ ትሄ ማግኘቱ ሻምበሉን ስላስደሰተው እጁን በእጁ እያሻሸ ሲመለስ በቀለች ከቦታዋ ላይ አልነበረችም ። ከገፁ ላይ የነበረው ፈገግታ ወዲያው ደበዘዘ ። የሚይዘ ውን የሚጨብጠውን አጥቶ ተቅበዘበዘ ። የት ሄደች ብሎ በመላኩ ላይ አፈጠጠበት ።

የሻምበሉ አራስ ነበር መሆን መላኩን አስደነገ ጠው ። ዘሎ የሚያንቀው መሰለው ። የበቀለች አለመኖር የሚያስቆጣ አልመሰለውም ። ሁኔታው ግን ስላስፈራው የሚናገርው ጠፋበትና ፥ "አሁን. . . አሁን ነበረች ፤ ወጣ አለች..." በማለት እየተርበደበደ የሄደችበትን አቅጣጫ በጣቱ ጠቆመው ።

ሻምበል ታምሩ ጊዜ ሳያባክን የተጠቆመውን አቅ ጣጫ ተከትሎ እየሮጠ ከሳሎኑ ወጣ ። በመጀመሪያ የበቀለችን የመኝታ ክፍል በር በርግዶ ገባ ። እሷ ግን አልነበረችም ። ከዚያም ክፍሎቹን አንድ በአንድ በየ ተራ አዳርሶ አጣት ። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ከቤት

እንዳልወጣች እርግጠኛ ነው ። በቀላሉ ከማትገኝበት አሳቻ ቦታ እንደ ተደበቀችም አውቋል ። ታመልጠኛለች የሚል ስጋት ባይኖርበትም ተሎ ካልደረሰባት ያል ታሰበ ችግር ይፈጠራል የሚል ጥርጣሬ አደረበት ። ቁጣ ቁና እየተነፈሰ ወደ ሳሎኑ ተመልሰና ፈልጎ እንዳጣት ልመ ላኩ ነገረው ። ልትደበቅበት ትችላለች የምትለው ቦታ ካለ ምራኝ አለው ።

መላኩ ግራ በተጋባ ሁኔታ ሻምበሉን ተመለከተና፡ "እስከዚህ ምን ያስቸኩልሃል ? መሬት ተከፍታ እትውጣት ፤ መፀዳጃ ቤት ስለሆነች ትንሽ እንጠብቃት" አለው ።

"ስለማትመጣ ጊዜያችንን በከንቱ እናጥፋ ።"

"ትመጣለች ፤ ለምን እትመጣም ?" አለ መላኩ በመገረም ።

"እንዴት አይገባህም ?"

"ምኑ ?" ሲል መላኩ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ ።

ሻምበል ታምሩ በመላኩ ጅልነት ተናደደና ፡ "እሱን እርሳውና ይልቅስ የተደበቀችበትን ቦታ ታውቅ እንደሆነ አሳየኝ ?" በማለት ቆጣ ብሎ ጠየቀው ።

መላኩ ፡ "እንዴት አይገባህም ?" የምትለው አጭር አረፍተ ነገር ሜንቅላቱን መታችው ። ከእንቅልፉም ቀስቀሰችው ። ጊዜ ሳያባክን ከሻምበሉ ጋር ወደ አቶ አደፍርስ መኖሪያ ቤት ሄዱ ። ሻምበሉ ከፍሉን ቀደም ሲል የፈተሸው በመሆኑ ከዚያ ውስጥ መኖሯን ተጠ ራጠረ ።

በክፍሉ ውስጥ ያለው ዘመናዊ አልጋ እንደ ተነ ጠረ ነው ። በከፍተኛ ወጭ የተገዛውም ልጋጅ ተገቢው ጥንቃቄ አልተነፈገውም ። ሌሎች ቁሳቁሶችም በአግባቡ ተይዘዋል ። የክፍሉም ዕዳኑ እንደ ተጠበቀ ነው ። የአል

ናቀች ፣ፎር ፎቶግራፍ ከአንደኛው ኮሞዲኖ ላይ ተቀ ምጦ ውብቷን ያንፀባርቃል ። የአቶ አደፍርስም ከግድግ ዳው ላይ ተንጠልጥሏል ። ሲገቡ ፊት ለፊት የሚታየው ከግድግዳው ጋር ተያይዞ የተሰራው ቁምሳጥን አምስት በሮች አሉት ። መላኩ በስተግራ በኩል የሚገኘውን የመ ጫረሻውን መዝጊያ ከፈተው ። ከውስጥ ያለውን ሁለ ተኛ በር ሻምበል ታምሩ ሲያይ ክቁምሳጥኑ በስተጀርባ ሌላ ክፍል መኖሩን አወቀና ፈገግ አለ ። መፀዳጃ ክፍል መሆኑን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደበትም ።

ሻምበል ታምሩ የሽንት ቤቱን የበር እጀታ ይዞ ለመክፈት ዲሞክር ዝግ ሆነበት ። መቆለፉ መጂያው ገባው ። በሞጂመሪያ ቀስ ብሎ እያንኳኳ መልሶ ጪጪ ብቅም ምንም አላ ። ትእግስቱ አለቀ በሀይል በሩን ቢደበድብም ከውስጥ የመጣ ድምፅ የለም ። በዚህ ምክ ንያት የሚያደርገው ጠፋውና ተንቀራጠጠ ። ምን ማድ ረግ ይኸላል እያለ አሰበ ።

መላኩም በበኩሉ ሌላ ትርፍ ቁልፍ ለመፈለግ እቃዎችን ቢያተራምስ ሳይቀናው ቀረ ። ወደ በሩ ተጠ ጋና ትንበሶ ብሎ በቁልፍ መክፈቻ ቀዳዳ ወደ ውስጥ ለመመልከት ሞከረ ። የብርሃን ጭላንጭል ለማየት ፍለ መቻሉ ቁልፉ ከውስጥ በኩል የተሰካ መሆኑን አረጋ ገጠ ። በዚህ ተበሳጭቶ በሩን እንስበረው የሚል ፀፅፃ አቀረበ ።

ሻምበል ታምሩ በሩን መስበር ቀላል እንዳልሆነ ተገንዝቦ አይሆንም አለው ። የተሻለ የመሰለውን ዘዴ ለመጠቀም ወደ በሩ ቀረበና ፡ "ወይዘሪት በቀለች ! ወይ ዘሪት በቀለች !ትሰሚኛለሽ! " በማለት እንደቡትን አለቅ ልቶ ጠራት ። መልስ ባለመገኘቱ ቅር አላለውም ነበርና፡ "በሩን ክፍተሽ ብንነጋገር ኣችግርሽ መጭትሄ ይፈልግ ለታል ሰግሽ ? ጥፋቱ ያንቺ ብቻ ልላልሆነ ይትርታ ይደ

ሩግልኛል ...” እያለ ቢለምናትም መልስ ሳትሰጠው ቀረች ። ሀሳቧን ብትቀይር ብሉ ጥቂት ጊዜ ዝም ብሉ ጠበቃት ። በመጨረሻ ተስፋ ቆረጠና ፣ “ለምን በከንቱ ራስሽን ታታልያለሽ! በፈቃድሽ እጅሽን ብትሰጪ ይሻልሻል ! እንቢተኛነቱ የኋላ ኋላ መዘዝ ያስከትላል!የምለው ይሰማሻል!ይሰማሻል! ” በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ቢወተውታትም መልስ ነፈገችው ። ቢቸግረው ከውስጥ መኖር አልመኖሯን ለማረጋገጥ ጆሮውን ከበሩ ላይ ደቅኖ ለማዳመጥ ሞከረ ። ያም ሆኖ የሰማው ምንም ነገር የለም ። ፀጥ እረጭ ማለቱ ከውስጥ ሰው ልመኖሩ አጠራጠረው ። ግን መላኩ ከውስጥ መቆለፉን ፣ ሲነግረው የፀጥታው ምክንያት ምን እንደሆነ ገባውና በቁጭት ራሱን ነቀነቀ ።

መላኩ ግን የሻምበሉ ሲጋት ምን እንደሆነ አልገባውም ነበርና ፣ “ማእርግ ከጠላባት ተዋት ! መጎለቱ ሲሰለቻት ሳትወድ በግድ ከፍታ እጅዋን በፈታዷ ትሰጣለች” አለው ።

ሻምበል ታምሩ በመላኩ የዋህነት ፈገግ ቢልም ያሰበው እንዳሰበው ባለመሳካቱ ተስፋ ቆርጦ ከአቶ አደፍርስ መኝታ ቤት ወጣና ወደ ሳሎን አዘገመ ። የሰል ኩን መነጋገሪያ አንሱቱ ቁጥሮቹን በጣቱ አሽከረከረ ። የሰልኩን ጥሪ የተቀበልውን ሰው በድምፅ ስላወቀው ፣ “የሙቶ አለቃ! ሻምበል ታምሩ ነኝ ! ...የአቶ አደፍርስን ቤት ታውቅ የለ !..በር መክፈቻ ..መስበሪያም በለው ብቻ የሆነ ነገር ባስቸኳይ ይዛችሁ እንድትመጡ ... እጠብቃችኋለሁ ... ስማ መቶ አለቃ ለአንቡላንስም ከፍል ይነገራቸው ! የሆነውን ነገር በግልፅ ባላውቅም ምናልባት መርዝ ሳትወልድ አትቀርም ” በማለት ተናገረና ስልኩን ዘጋው ።

አስራ አንድ

በቀለች ከወላጅ እናቷ ስትለይ ልጅ ብትሆንም በመሃላቸው የጠበቀ ግንኙነት ነበር ። በተገናኙ ቁጥር ከእናትነት ፍቅር ሌላ በአቶ አደፍርስ ላይ ያላቸውን ጥላቻ አካፍለዋታል ። ነፍሰ እያወቃች ስትሄድ ስለ አባቷ በግፍ መገደል ካለመታከት አጫውተዋታል ። አሟሟታቸውንም በሚዘገንን ሁኔታ ደጋግመው ተርከውላታል ። ለዚህ ሁሉ አመፅ ተጠያቂው ጨካኙ አጎትሽ ነው ብለው አሳምነዋታል ። አንቺና እኔን ያለያየንም ያባትሽን ድርሻ ላለማካፈል ሲል ነው እንጂ ላንቺ አስቦ አይደለም ብለዋታል ። በዚህ ምክንያት አቶ አደፍርስን እየፈራችና እየጠላች አደገች ። እንደ አባት ሳይቀርቧት ፣ እንደ ልጅ ሳይመለከቷት ፣ ስሜቷን ቀርበው ሳይረዱላት ግደጓ ይበልጥ ተጠራጣሪ አደረጋት ። በጥፋቷ የሚደርስባትን ቅጣት ወደ ሌላ እየተረጎመች ስሜቷን ለመጥፎ ነገር ቃበዘች ። ግን አቶ አደፍርስ የሚገባትን ፍቅር ከመንፈግ በስተቀር ያደረሱባት በደል የለም ። እርግጥ በሷ እድሜ ክልል እንደሚገኙት ኮረዳዎች ለማጌጥም ሆነ ለመሽቀርቀር የነበራትን ፍላጎት አላሟሏላትም ። እንድትሞላቀቅም እድል አልሰጧትም ። እሷ ግን ጥቃቅኑን ነገር በአእምሮዋ እያጠራቀመች ልሳቸው ያላትን ጥላቻ እሽሩሩ ብላ አዳበረች ። የጥፋት መልእክተኛ የሆኑት እናቷ በመጠጥ ሱስ ተጎሳቁለው ከሰውነት ውጭ ሆነው እለተ ሞታቸው ሲቀርብ የነገር መርዝ በአንጎሏ ውስጥ ነሰነሱባት ። ያልመረጠችውን የህይወት ጎዳና እንድትከተል አደረጓት ። መንፈሳቸው እጅዋን ይዞ ወደ ጥፋት መራት ።

አንድ ቀን ማታ አቶ አደፍርስ ከልዩ ክቡላቸው ሰነዶች ሲያገላብጡ በቀለች ፀሩን አንኳኩታ ገባች ። ቀና ብለው በፈገግታ ተመለከቷት ። ይህም የልብ ልብ ሰጣት ። ፍርሃቷንም አስወገደላት ። ጥሩ ጊዜ እንደ መረጠችም ተሰማት ። ፍላጎቷም ግቡን የመታ መሰላት። ሀሳቧን በአንድነት ሰበሰበችና ፥ "አባዬ ፥ አንድ ነገር ላስ ችግርህ!" አለቻቸው ግድግዳውን ተደግፋ ።

"ምን የሚሉት ችግር!" አሉ አቶ አደፍርስ ።

"ችግር እንኳን አይደለም ብቻ ..."ብላ ሳትጨርስ ።

"ላስቸግርህ ግለት እኔ እንደማውቀው ከችግር ጋር የተያያዘ ነው ፤ ካልሆነም ጥሩ ፤ ጉዳይሽ ምን ኖሮር?" አሏት እንደ ቀልድ አድርገው ።

"እሱስ ቀላል ነው" አለች ጣቷን እንደ ሀፃን እየ መጠጠች ።

"ንገሪኛ!' አሉ ።

"መኪና ..." ብላ አረፍተ ነገሩን ሳትጨርስ ዝም አለች ።

"መኪና ነው ያልሽው?" አሉ የሰሙትን በመጠ ራጠር ።

"አዎ" አለች አቀርቅራ ።

"መኪናችን ምን ሆነ?" ብለው ጠየቋት ።

"አንድ ትንሽ መኪና ብትገዛልኝ" አለች ስትፈራ ስትቸር ።

አቶ አደፍርስ እሽም እምቢም የሚል መልስ ወዲ ያው አልሰጧትም ። በጉዳዩ ላይ ጥቂት አሰቡና አሰፈ

በቀለች ትምህርቷን ጨርሳ ስራ ከያዘች በኋላ ከአ ጎቷ ቤት ለመውጣት አሰበች ። የአባቷን ሀብት ተካፍላ በአለም በደስታ ለመኖር አቀደች ። በገንዘቡ የምታደር ገውን ማውጣት ማውረድ ጀመረች ። የምኞቷን አዳ ግስ በሰፈው ዘረጋች ። ደፍራ ድርሻዋን ለመጠየቅ ግን ልብ አጣች ። እንዲህ አይነቱን ነገር ከአቶ አደፍርስ ፊት ለማንሳት ፈራች ። ብዙ ጊዜ ቆርጣ ተንስታ ስታያ ቸው ትሸበርና ሀሳቧን እንድትቀይር ትገደዳለች ። በሀይል እንዳትጋፈጣቸው የአናቷ ቃል ትዝ ይላታል ። በጥቅም በኩል የመጣበትን ካለ ርሀራሄ ያጠፋል ያሏት ከጭ ንቅላቷ ውስጥ ይደውላል ። ስለዚህ መክሰሱ መዘዝ እንደሚያስከትልባት ይሰማታል ። ከትላልቅ ሰዎች ጋር ካላቸው ግንኙነት አንፃር በዘግም ለመርታት ያላትን እድል እንድትጠራጠር አድርጓታል ። ችግሯን በጣም ለሚቀርቧት በምስጢር አጫውታ አርፈሽ ተቀመጭ ብለዋታል ። ሌላ ምርጫ አልነበራትምና ልጂቷን አምታ ምኞቷን ገድባ ተቀመጠች ።

አቶ አደፍርስ በብቸኝነት ሲኖሩ ቆይተው አሰና ቀችን በህግ አገቡ ። በጉሮአቸውም ደስተኛ ሆኑ ። መዝ ናናትን የዘወትር ተግባራቸው አደረጉ ። በንፋሳነታቸው ያልታወቁትን ያህል ገንዘብ መበተን ጀመሩ ። ዘመናዊ መኪና ገዝተው ለአዲሷ ሚስታቸው ሰጡ ። በቀለችንም ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ አቀረቧት ። የወንድሜ ልጅ እያሉ ከአስናቀች ጓደኞች ጋር አስተዋወቋት ። ለመጀመሪያ ጊዜ በፍቅር አይን ተመለከቷት ። ሰብአዊ ክብሯንም አወቁላት ። እሷም እንደ አሙሬ ትፈራቸው የነበሩትን ሰው ቀስ በቀስ ለመደምቸው ። በይበልጥ አስ ናቀች እንዲቀራረቡ እደረገቻቸው ። ሁኔታው ስል ፈቀደ እንደ ልጂ አንጋገረቻቸው ። በተልኝ ይህን እጋጣሚ በቸልታ ልታልፈው ስላልፈለገች እመቾ ቀን መበቀች።

ላጊ ከመሰለሽ የማይገባበት ምክንያት አይኖርም አሏት ። በመጀመሪያ ግን መንዳቴን ተማሪ ብለው መክሯት ። ለሷ ደህንነት ያሰቡ በሚመስል ሁኔታ በጥንቃቄ ተለ ማመድ ብለው አሰናበቷት ።

በቀለች አጎቷ የሰጧትን ተስፋ አንጠልጥላ መኪና የመንዳት ትምህርት ጀመረች ። ከአራት ወሮች በኋላ ለፈተና ስትቀርብ በመደንገጫ ሳታልፍ ቀረች ። ከአ ስራ አምስት ቀን በኋላ እንድትመለስ ተቀጠረች ። ደንግጠሽ ነው ያላት አስተማሪዋ ነው እንጂ ማሽከር ከሩንም በሚገባ አላወቀችበትም ነበር ። ስለዚህ አምስት ጊዜ ያህል ተፈትና በስድስተኛው አልፈሻል ስትባል ከደስታዋ ብዛት ሀሊናዋን ልትስት ምንም አልቀራት ። የራሷን መኪና ስታሽከረክር እንደ ሰመመን ታያት። የዚያ እለት ማታ አቶ አደፍርስን ጠብቃ የምስራቹን ነገረቻቸው ። ደስ ብሎኛል ደስ ይበልህ አለቻቸው ። ጥሩ ነው በሚል ቃል ብቻ የደስታዋ ተካፋይ መሆናቸ ውን ገለፁላት ። ከአነጋገራቸው ለጉዳዩ ይሀን ያህልም ክብደት እንዳልሰጡት ግን አልገባትም ። ከአሁን አሁን የምትመርጭውን መኪና ንገሪኝ ይሉኛል ብላ አይን አይናቸውን ስታይ ዝም አሏት ። አርእስት ለውጠው ስለሌላ ነገር ጠየቋት ። በትእግስት ብትጠብቅም ከዚ ያች እለት ወዲህ የመኪና ነገር አልተነሳም ። በዚህ ምክንያት ሊድን የነበረው ቁስሏ እንደገና አመረቀዘ ። ጥላቻዋም ስር ሰደደ ።

በቀለች በአጎቷ ሚስትና በመላኩ መሀል ያለው ግንኙነት ጤነኛ እንዳልሆነ ለመረዳት ጊዜ አልወሰደ ባትም ። ግን ምንም የማታውቅ መስላ ለመታየት ሞከ ረች ። አስናቀችም እንዳትጠራጠራት ወዳጅነቷን አጠ ናከረች ። ኤድፍጣ ቀኗን ጠበቀች ። አስናቀች በየዋህነት

መፀነሷን ስትነግራት በዘዴ ጉድጓድ መቆፈር ጀመረች ። በአባትና በልጅ መሃል ውዝግብ እንዲነሳ እሳት ጫረች። እንዳይበርድም የተቻላትን አደረገች ። ፍላጎቷን የምት ፈፅምበትን አመቺ ሁኔታ ፈጠረች ። የአባቷን ሀብት እጅዋ ለማድረግ ከዚህ የተሻለ አድል እንደማይገጥማት አወቀች ። ሁኔታው ሲፈቅድላት በአቶ አደፍርስ ደም ታጠበች ።

በቀለች ወንጀሉን ፈፅማ ከአቶ አደፍርስ ክፍል ስትወጣ ከአስናቀች ጋር በድንገት ተገናኙ ። ሁለቱም ደንግጠው ቀጥ ብለው ቀሩ ። ወዲያው በቀለች የሆ ነውን ነገረቻት ። አስናቀች የሰማችውን አላመነችም ነበርና ተጠራጠረቻት ። ከዚያም አንቺ ነሽ የገደ ልሻቸው ብላ ወነጀለቻት ። በቀለች እኔ አይደለ ሁም ብላ ካደቻት ። እንዳልተቀበለቻት ስትረዳ ግን ከኔ ይልቅ ምክንያት ያላችሁ አንቺና ውሽማሽ ናችሁ ብላ አስፈራራቻት ። አቶ አደፍርስ በጤና መታወክ መውለድ እንደማይችሉ አድርጋ በሀሰት ሽብር ለቀቀች ባት ። ማንም ይግደለው ላንቺ የሚበጅሽ ከኔ ጋር መስ ማማት ነው አለቻት ። ፖሊሶችም ቢሆኑ ካንቺ ይልቅ የኔን ቃል እንደሚያምኑ ልታውቂው ይገባል ብላ አስ ጨነቀቻት ። ጥቅማቸውን በጋራ ለመጠበቅ ማድረግ የሚገባትን በቅጥ አስረዳቻት ።

አስናቀች ዙሪያው ገደል ሆነባት ። ከዚህ ፈተና ውስጥ መውጫ ቀዳዳው ጠበባት ። ጥርጣሬ እንጂ የወ ንጀሉ ፈፃሚ ግርማ ይሁን በቀለች አላወቀችም ። እር ግጠኛ ባልሆነችበት ነገር ደግሞ ጣጣ ማምጣት አልፈ ለገችም ። የበቀለችን ሀሳብ መቀበል ለሷም ሆነ ለመላኩ የሚጠቅም ሆኖ አገኘችው ። ከዚህ የተሻለ አማራጭ አል ነበራትምና ተቀበለችው ።

ሻምበል ታምሩ ብቦታው እንደነበረ ሰው የመንጀሉን አፈፃፀም ሲተርክ በቀለች መልእክቱ ለፅ መሆኑ በግልፅ ታወቃት ። ይህም አስናቀች ራሷን ልግዳን ስትል ምስጢራችንን ለጠበቃው በዝርዝር አስረድታዋለች የሚል ቁጭት አደረባት ። ክዚህ ይደርሳልነብላ ባትገምትም ሴፈው መፍረክረኩ ከገባት ግን ውሎ አድሯል ። ምስጢሩ በይፋ ሲታወቅ ፀወጥመድ እንደ ተያዘ አውሬ ከፋኛ ጩኔቃት ። ያም ቢሆንም ስሜቷን ተቆጣጥራ መሸበሯ እንዳይታወቅባት ልማስመሰል ሞከረች ። በቁጥጥር ስር ውሎ የሷቃይ እድሜን ማራዘም ደካማነቱ ነው ብላ እጅዋን ላለመስጠት ወዲያው ወሰነች ። ከሻምበሉ ፊት ለጥቂት ጊዜ የምትሰወርበትን ዘዴ ስታሰላ ሰል የሰልኩ ጥሪ መንገድ ከፈተላት ። ይህም ምርጫዋን ለመፈፀም የምትችልበትን ሁኔታ ፈጠረላት ።

አ ስ ራ ሁ ለ ት

መርማሪ ፖሊሶች በቀለች የተደበቀችበትን የመፀዳጃ ክፍል በር ሰብረው ሲገቡ ከገላ መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ሞታ መገኘቷን ብዙዎቹ ሰምተዋል ። ህይወቷን በራሷ እጅ ለማጥፋቷም በማያጠራጥር ሁኔታ ተረጋግጧል ። የዚህን ውስብስብ ወንጀል መጨረሻ ለማወቅ ክመቸውም ጊዜ ይበልጥ ፍርድ ቤቱ ውስጥ ሰዎች በብዛት ተገኝተዋል ። አቃቤ ህግም ሆነ ጠበቃው ማን ደፍሮ ፀታቸውን ይዘዋል ። ግርማ የቆዳ ጃኬትና ጥቁር ሱሪ ለብሶ ከተመደበለት ቦታ ተቀምጦ ማርታን በእይኑ ፈልጎ መኖሯን አረጋገጠ ። ለመጀመሪያ ጊዜ የእንጀራ አባቱ ክእናቱ ጋር መምጣታቸውን ተመለከተ ።

ሰውየው ክወዛኒ ቤት ተመላልሰው የጠየቁት በመሆኑ ክፍርድ ቤት ዓለመምጣታቸው ቅሬታ አላደረበትም ነበርና ሊያያቸው ደስ አለው ። በተጨማሪም የእንዳንድ ወዳጆቹ መኖር የዋፊል ምርኩዝ ሆነውና ተስፋውን አለመለመው ።

ዳኛው ግራ ቀኙን ተመልከተው ፣ "ከባለሙያዎች በፅሁፍ የደረሰን ምስክርነት እንደሚያመለክተው የወይዘሮ አስናቀች ህይወት የጠፋው ራሱን በቻለ መርዝ እንጂ በእንቅልፍ መድሃኒት እንዳልሆነ አረጋግጠል ናል ። ስለዚህ ቀደም ሲል የዚህ ማስረጃ መቅረብ አስፈላጊነት የታመነበት ስለሆነና እንዲሁም የተከሳሹ ጠበቃ ለመከላከያ ወሳኝነት ይኖረዋል ስላለ በዚህ በኩል ያለውን አቋም ለፍርድ ቤቱ ያስረዳ" ብለው አዘዙ ።

ግንደፍሮ ተነስቶ እጅ ነሳ ። ካሳውን አስተካክሎ ወደ መሃል ገባና ፣ "አቶ አደፍርስንም ሆነ ባለቤታቸውን የገደለችው በቀለች መንገሻ እንደሆነች ግልፅ የሆነ ይመስለኛል ። ሆኖም በቀለች ወንጀሉን ለምንና እንዴት እንደ ፈፀመች ለፍርድ ቤቱ ማሳየት እፈልጋለሁ ። አስናቀች ከባልቤቷ ክአቶ አደፍርስ መውለድ አለመቻሏን በቀለች በሠሰት አስመስላ ስለነገረቻት ብቻ ካለ ምንም ጥርጣሬ ፅንሱ የመላኩ ይሆናል ብላ በስሜት አመነችበት ። በሌላ በኩል ደግሞ አላማዋ ግቡን ይመታ ዘንድ በመላኩና በአስናቀች መሃል ያለውን ምስጢራዊ ግንኙነት ለተከሳሹ ትገልፅለታለች ። አቶ አደፍርስ በመጣቷ ሚስታቸው ፍቅር ታውረው ስለነበር በስተጀርባ ቸው የሚፈፀምባቸውን ደባ አምነው ሊቀበሉ ባለመፍቀዳቸው በአባትና በልጅ መሃል አለመግባባት ይፈጠራል ። ከቤቱ ውስጥ የተከሰተው ሁኔታ አስናቀችን የህ

ሊና እረፍት ነስቷት ከዛሬ ነገ ተዋረድኩ እያለች ሰት ጨነቅ ከረመች ። አጋጣሚ ሆነና የበቀለች እጅ በአቶ አደፍርስ ደም ሲቀላ አየች ። ሁለቱም የየራሳቸውን ሀልውና ለመጠበቅ ሲሉ በተንኮል የጋራ ግንባር ፈጥ ረው ተከሳሹ የሚወነጀልበትን ዘዴ ወዲያው ቀየሱ ...

"እስናቀች በሙያው እንደሰለጠነ የመድረክ ሰው ያየችውን በማየቷ የደነገጠች መሰላ እሪ ብላ ጮኸች ። ሀሊናዋን ሳትስት የሳተች ሆና በመቅረቧ መላኩ እው ነቱን እንዳያውቅ ፥ የወንጀሉንም ትክክለኛ ገፅታ እንዳ ይከሰትለት በሀሰት መጋረጃ አይኑን ሸፈኑት ። በአንድ ድምፅ ተከሳሹን በሀሰት ወንጅለው መሰከሩበት ። የገደለ ይሞታል ሲባል ሰምተዋልና የጥቅም ሚዛናቸውን በመ ጠበቅ በቀለች ያባቷን አስናቀችም የባለቤቷን ንብረት ሊከፋፈሉ እቅድ አወጡ ። ሆኖም እውነትን ማፈን የሚችል ሀይል የለምና ሴራቸው ቀስ በቀስ እየተፍረከረከ ሲሄድ አንዷ ለሌላዋ የነበራት ታማኝነት መሸመሩን ለቀቀ ። አስናቀች ለችግሯ መፍትሄ ለመሻት የህግ አማ ካሪ ፈለገች ። 'አባብ ለአባብ ይተያያል ካብ ለካብ' ነውና በቀለችም ምስጢር ሳይዝረከረክ በወቅቱ ርምጃ ስለወ ሰደች አስናቀች ወደ ሙታን አለም በእንባ ተሸኘች ...

"ለዚህ ሁሉ አመፅ መሰረታዊ መነሻ ምንድነው ? የነገሩን አመጣጥ ወደኋላ መለስ ብለን እንመልከት ። አቶ አደፍርስና ወንድማቸው አቶ መንገሻ የበቀለች አባት በውርስ ምክንያት በመሃላቸው ጠብ ይፈጠራል ። ከረ ጅም ጊዜ መግት በኋላ በሀገር ሽማግሌዎች አስታራቂ ነት ከስምነት ሳይ ይደርሳሉ ። ሆኖም ግን ንብረቱን ሳይካፈሉ አቶ መንገሻ ባልታወቀ ሰው በድንገት ይገ ደላሉ ። የወንጀለኛው በውል አለመታወቅ ደግሞ አደ ፍርስን ከማስጠርጠር አልፎ ነፍሰ ገዳይ እስክ መባል

ያደርሳቸዋል ። ግን ማስረጃ የሌለው ነገር ሁሉ ሀሜት ነውና በሀሜትነቱ ይቀራል ...

"ውሸት ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ሲነገር እንደ እው ነት ይቆጠራል ፤ የሚሉት ዘይቤ አለና በቀለች በአፍላ እድሜዋ ከእናቷ የሰማችው መሰረተ ቢስ አሉባልታ በተሰዋሪ ሀሊናዋ ውስጥ ተደብቆ ስነ ልቦናዊ ተፅእኖ ያሳድርባታል ። በተጨማሪም ፍቅር አልባ አስተዳደጓ ለዚህ ድክመቷ አስተዋፅኦ ማድረጉ አይጠረጠርም ።በተ ለይ ደግሞ ለአቅመ ሄዋን ከደረሰች በኋላ በተለያዩ ምክ ንያቶች ምናልባት አቶ አደፍርስ ፍላጎቷን ለማሟላት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ከሆነ ይበልጥ እንድትጠላ ቸው ገፋፍቷታል የሚል ግምት አለኝ ። ወይም የአባ ቷን ሀብት እንዲሰጧት ጠይቃቸው ለማካፈል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተውም ይሆናል ። ያም ሆነ ይህ ግን የአቶ አደፍርስ ሰፍሳፋነት ያባቷን ሞት ምስጢርነት ከንብረ ታቸው ጋር በቅርብ የተያያዘ እንዲመስላት ስላደረጋት ጥላቻዋ ተንኮልን ወልዶ ወደ ጥፋት መራት ። ምንጩ ይህ ቢሆንም ግንኙውንም ነገር በተለይም ወንጀል ለተ ግባራዊነቱ አጋጣሚ ይፈልጋልና አቶ መላኩ የሀሰት ካባ ደርቦ አቶ አደፍርስ ቤት መምጣቱ ሁኔታዎችን አመቻችቶላታል ። በዚህ ተገፋፍታ የጥፋት እጅዋን ዘር ግታ ክቡር ህይወት ካለምንም ሰብአዊ ርህራሄ ቀሰፈች ግን ከፋትን ያመጡ ሁሉ መከራን ይወልዳሉና ለሌሎች የጋበዘችውን መራር የሞት ፅዋ እሷም በተራዋ ሳትወድ በግድ ተጎንጭታ ህይወቷን በራሷ ውሳኔ አጨለመች ። ሀቁ ይህ ነውና ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በወንጀሉ ውስጥ ምንም አይነት ሚና አለመጫወቱን ተገንዝቦ በነፃ እን ዲያሰናብተው በትህትና እጠይቃለሁ" ብሎ ቀመጠ ።

ግንደፍር በፍርድ ቤቱ ውስጥ የነበሩትን ልዎች ኤድናቆት ተንናዐፈ ፤ በአርቆ አስተዋይነቱም ተወደሰ ። በቀለች ከህግ ፊት ተሰውራ ራሷን በራቂ መግደ ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ወንጀለኛዋ እሷ መሆና በሁ ሉም ዘንድ ታውቋል ። ግን ግንደፍር ከመነሻው እስከ መጨረሻው የጥፋት መልእክተኛው ሶስተኛው ሰው ነው ብሚለው አቋም ፀንቶ እውነቱ ላይ መድረሱ ብዙዎቹን አስገርሚቸዋል ።

ሻምበል ታምሩ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከአጠ ገቡ ተሰውራ ህይወቷን ማጥፋቷ ቢቆጨውም ቅድ በከንፈር ቀለም ከመስታወቱ ላይ ፥“ ኣጥፍቻለሁ ፤ ለጥ ፋቴም ተመጣጣኝ ቅጣት ወስኛለሁ” የሚለው ታል ወንጀለኛነቷን አረጋግጦለታል ። እሷም ሆነች አስናቀች ህይወታቸውን ያጡት በተመሳሳይ መርዝ ነው የሚል ጥርጣሬ አድሮበታል ። የምርመራውም ውጤት ይህንኑ እንደሚያረጋግጥ ተስፋ አድርጓል ። ለአቃቤ ህግም ሁኔ ታውን በዝርዝር አስረድቶት በወንጀሉ ግልፅነት ተማምነውበታል ። ግን አስናቀች ከተጋለጠች በኋላ እንዴት ልመላኩ የምታውቀውን ምስጢር ላታካፍለው ቀረች የሚለው ጥያቄ በህግ አዋቂዎች ዘንድ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተለያየ አስተያየት ቀርቦበታል ። ለወንጀሉ ተባባሪ መሆኗን መላኩ ካወቀብኝ ሊጠላኝ ይችላል የሚል ጥርጣሬ አድሮባት ይሆናል ያሉም ነበሩ ። በተ ለይ ግን እንደ ታሰበው ግርማ በአባቱ ሞት ተጠያቂ ሆኖ ከተፈረደበት መላኩ የሚያውቀውን ምስጢር ተገን አድርጎ ሰላም አይሰጠኝም በሚል ፍርሃት ነው የደበቀ ችው የሚለው አስተያየት ግን በብዙዎች ዘንድ ተቀባ ይነት አግኝቷል ። ይህም ግምት እንጂ ከሷ ከራሷ በስ ተቀር ትክክለኛ ምክንያቷን የሚያውቅ ሰው የለም ።

ዳኛው እንደ ግንዛቤም ሰው ቀደም ሲል የተፈ ጠረውን ሁኔታ ፀያውቁም የፍርድ ቤቱን ደንብ ግጂ ላት አስፈላጊ በመሆኑ አቃቤ ህግ በጉዳዩ ላይ አስተ ያየት እንዳለው ጠየቁት ።

“የልኝም” ሲል መለሰላቸው ።

ዳኛው ክሁለቱም ወገን አከራካሪ ነጥቁ አለመኖ ሩን አረጋግጠው የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለማሰማት ዝግ ጁነታቸውን ሲገልፁ ተከሳሹ ግርማ ተነስቶ ቆመ ። ሁሉም ፀጥ ብሎ በአንክሮ ለማዳመጥ ጀርውን አት ንቶ ጠበቀ ። ዳኛው ከፊት ለፊታቸው የተዘረጋውን ሩይል አስተካከሉና “ፍትህ እንዳይዛባ ፤ ፅዐአዊ ክብር አለአግባብ እንዳይደፈር ፤ የእውነት ልእልናም በሀሰት እንዳይታፈን ፤ ፍርድ ቤቱ በተጣለበት ከፍተኛ ሀላፊነ ትና አደራ ፤ በአቃቤ ህግም ሆነ በተከሳሹ ጠበቃ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ሲመረምርና ህጋዊ ክርክሩንም በጥ ሞና ሲከታተለው ቆይቷል ። ለወንጀሉ መፈፀም መነሻ ምክንያት ነው ተብሎ ክስ የተመሰረተበት ጭብጥ በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈ ሲሆን ተከሳሹም ወንጀሉን ለመ ፈፀሙ በማያጠራጥር ሁኔታ አልተመሰክረበትም ። በተ ለይም የሁለቱ የህግ ምስክሮች በድንገት ከዚህ አለም ፀሞት መለየት ቀደም ሲል ተከሳሹ ፈፀመ ከተባለው ወንጀል ጋር የቅርብ ግንኙነት ሳይኖረው አይቀርም የሚል ግምት በፍርድ ቤቱ ላይ አሳድሯል ። ስለዚህ በተቀነባበረ የተንኮል ሴራ ሰላማዊ ሰው ባልፈፀመው ጥፋት ተጠያቂ እንዲሆን ለማድረግ የተሞከረ ስውር ደባ መሆኑን በመገንዘብ ይህ ፍርድ ቤት በዛሬው ቀን ተከሳሹ ግርማ አደፍርስን በነፃ አሰናብቶታል ” ፀማ ልቅ ፍርድ ሰው ።

የተሰበሰበው ህዝብ ስሜቱን መቆጣጠር አቃተ ውና በል እንደ ተባለ በአንድነት ተነስቶ አጨበጨበ ። ሆቅን የሚነድል ሀይል የለም አለ ። ፍትህ በሚገባ ተበየነ ብሎ ሲያወካ የሚደግመዋ ጠፋና ፀጥታው ደፈረሰ ። ፍርድ ቤቱ ውስጥ ትርምስ ሆነ ። የግርማ እናት እልልታ ቸውን አቀለጡት ። አጠገባቸው ያገኙትን ሁሉ እያቀፉ ሳሙ ። ግርማ ለጠበቃው ያለውን አድናቆት ገለፀለት ። ከልብ የመነጨ ከፍተኛ ምስጋናም አቀረበለት ። ማርታ ከደስታ ብዛት ስቃይ ይዞ እየተናነቃት ሰዎችን ካለ ምንም ይሉኝታ እየጣሰች አልፋ ከግርማ አንገት ላይ ተጠመጠመች ። ባደባባይ ፍቅሮን መግለፅ ለባህሉ ያል ተለመደ እንግዳ ነገር ቢሆንም በትዝብት አይን አል ታየችም ። እሷም ብትሆን በዚያ ወቅት ለማንም ግድ አልነበራትም ። ግርማ እንኳን ደስ ያለህ በማለት መል ካም ምኞታቸውን የገለፁለትን ሁሉ አመስግኖ ከማርታ ጋር እንደ ተቃቀፉ ከፍርድ ቤቱ ወጡ ።